ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 225 ሚያዝያ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# ምክክር- የዘላቂ ሠላም ሁነኛ መፍትሔ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ በሁሉም መስኮች ትልልቅ ስኬቶችን አስመዝግባለች፡፡ እነዚህ ውጤቶች ግን አልጋ በአልጋ በሆነ መንገድ የተገኙ አይደሉም፡፡ በብዙ ተግዳሮቶችና ፈተናዎች ውስጥ እንጂ፡፡

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስተዋለው የሠላም መደፍረስ እንደሀገር በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ተግዳሮቶች አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

ሠላም የሁሉም ነገር መሠረት እንደመሆኑ፣ የሚስተዋለውን የሠላም እጦት በጊዜ መፍትሔ መስጠት ካልተቻለ ትልቅ ሀገራዊ ቀውስ ሊያጋጥም እንደሚችል የዘርፉ ምሑራን ማሳሰብ ከጀመሩ ውለው አድረዋል፡፡

መንግሥት ጥያቄ አለኝ የሚል አካል ሁሉ ለውይይት ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ እንዲመጣ ተደጋጋሚ ጥሪ አቅርቧል፡፡ ከየትኛውም ወገን ጋር ለመወያየትና ችግሮችን ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነትም አሳውቋል፡፡ ሀገራዊ የምክክር

ምክክር - የዘላቂ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በሸገር ከተማ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለ115 ሺ ወጣቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

ገጽ 4

## ክልሉ ከሮዝመሪና በርበሬ ምርቶች ከ10 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ አግኝቷል



**ማሕሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት እሴት የተጨመረበትን 13 ሺ 786 ኩንታል በርበሬ እንዲሁም 22 ሺ 760 ኩንታል ሮዝመሪ ወደ ተለያዩ ዓለም ሃገራት በመላክ 10 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘቱን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አስታወቀ፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ማዕረግ የግብርናና ገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ዑስማን ሱሩር ለኢፕድ እንዳስታወቁት፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ወደ ተለያዩ የዓለም ሃገራት ከላካቸው የግብርና ምርቶች መካከል እሴት ከተጨመረበት 13 ሺ 786 ኩንታል በርበሬ 6 ነጥብ 1 ሚሊዮን ዶላር እንዲሁም ከ22 ሺ 760 ኩንታል ሮዝመሪ 4 ነጥብ 1 ሚሊዮን ዶላር በድምሩ 10 ነጥብ 2 ዶላር ማስገባት ችሏል፡፡

እንደአቶ ዑስማን ገለፃ፣ የክልል መንግሥት 'በአዲስ አስተሳሰብ፣ አዲስ ምዕራፍ፣ አዲስ ተስፋ ለአዲስ ክልል' በሚል የልማት ንቅናቄ ከዚህ ቀደም ያልተለመዱ የተለያዩ

ክልሉ ከሮዝመሪና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር)

## የውሃና ኢነርጂ ተደራሽነትን ለማሳደግ ለሚሰማሩ ድርጅቶች ድጋፍ ይደረጋል

- 71 ሚሊዮን ዜጎች ንጹሕ የመጠጥ ውሃ እያገኙ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የውሃ ኢነርጂ ተደራሽነትን ለማሳደግ ለግልና ልማታዊ ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በአሁኑ ጊዜ 71 ሚሊዮን ዜጎች ንጹሕ የመጠጥ ውሃ

የውሃና ኢነርጂ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






አቶ በየነ ተዘራ

# የሬሚዲያል ፈተና ከሰኔ ወር መጀመሪያ ጀምሮ ይሰጣል

## ከ78 ሺህ በላይ ተማሪዎች የሬሚዲያል ትምህርት እየወሰዱ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የሬሚዲያል ፈተና ከሰኔ ወር መጀመሪያ እስከ 15 ባሉት ቀናት በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች ልማት ዴስክ ኃላፊ አቶ በየነ ተዘራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዘንድሮውን የሬሚዲያል ፈተና ከሰኔ ወር መጀመሪያ እስከ 15 ባሉት ቀናት በሁሉም የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ለመስጠት እየተሠራ ነው፡፡

ባለፈው ዓመት የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ ፈተናውን በሁሉም የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ ለመስጠት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ በየነ፤ ፈተናው በኦንላይን፣ በኦንላይንና በወረቀት አልያም በጥብቅ ቁጥጥር በወረቀት ለመስጠት ታቅዶ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ባለፈው ዓመት ከነበሩ ክፍተቶች ትምህርት በመውሰድ ዘንድሮ ፈተናው በጥብቅ ቁጥጥር በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ብቻ ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን በመግለጽ፤ ፈተናው በማዕከል ደረጃ በጥብቅ ቁጥጥር ተዘጋጅቶ የሚሰጥና የሚመራ እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡

የሬሚዲያል ትምህርት ዙሪያ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመወያየት ወደ ሥራ መገባቱን ጠቅሰው፤ ከ70 በመቶ የሚዘጋጀውን ፈተና ከሰኔ ወር መጀመሪያ እስከ 15 ለመስጠት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በዘንድሮው ዓመት 32 ሺህ 500 ተማሪዎች 50 በመቶ በላይ በማምጣት በቀጥታ ዩኒቨርሲቲ ገብተው መደበኛ ትምህርት እየተከታተሉ እንደሚገኝ አስታውሰው፤ ከ78 ሺህ በላይ ተማሪዎች በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ሬሚዲያል ትምህርት እየወሰዱ ይገኛል ብለዋል፡፡

የሬሚዲያል ትምህርት ከታኅሣሥ ጀምሮ እስከ ሰኔ መጨረሻ እየተሰጠ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ውጤታቸው 30 በመቶ በዩኒቨርሲቲዎች የትምህርት ሂደትና 70 በመቶ በማዕከል እንደሚዘጋጅ አስረድተዋል፡፡

የሬሚዲያል ትምህርት ተማሪዎች እራሳቸውን አሻሽለው ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ ዕድል ፈጥሯል ያሉት አቶ በየነ፤ በተማሪዎች የትምህርት ዝግጅትና ውጤት ላይ መሻሻል ማምጣቱን ጠቁመዋል፡፡

የሬሚዲያል ትምህርት የዩኒቨርሲቲዎችን ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደትን ውጤታማ ያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ተማሪዎች በቁጭት አንባቢና ጠያቂ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የስብዕና፣ የሥነ ልቡና ማነቃቂያ ትምህርት እየተሰጣቸው እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

# ፕሮጀክቱ ከአካባቢ ጋር የሚስማማ የምርት ሂደት እንዲኖር ያደርጋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የጨርቃጨርቅና አልባሳት ፋብሪካ ተረፈ ምርቶችን በአግባቡ ለማስወገድ የሚያስችለው ፕሮጀክት ከአካባቢ ጋር የሚስማማ የምርት ሂደት እንዲኖር እንደሚያደርግ ተገለጸ፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች ከአካባቢ ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ ምርቶችን በማምረት ዘላቂ ተወዳዳሪ የሚሆኑበትን ፕሮጀክት ይፋ አድርጓል።

በፕሮጀክቱ ማስጀመሪያ ወቅት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ሚልኬሳ ጃጋማ (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ዘርፉ በኢትዮጵያ በከፍተኛ እድገት ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህ ፕሮጀክት ተግባራዊ ሲደረግ የፋብሪካ ተረፈ ምርቶችን በአግባቡ በማስወገድ፤ ምርታማነትን በማሳደግ፤ ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠርና ኢንቨስትመንት በመጨመር ከአካባቢ ጋር የሚስማማ የምርት ሂደት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

የጨርቃጨርቅና አልባሳት ዘርፍ በዓለም ላይ በካይ ከሚባሉ ዘርፎች ውስጥ አንዱ መሆኑን ያነሱት ሚልኬሳ (ዶ/ር)፤ ፕሮጀክቱ የአየር ብክለትን በመከላከል የመሬት፣ የውሃና የዜጎችን ደኅንነት በመጠበቅ ለኅብረተሰቡ ተስማሚ ምርቶችን ለማቅረብ እንደሚያግዝ ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም እንደሚያስችል ጠቁመው፤ ለቀጣይ አምስት ዓመታት በዘርፉ በተመረጡ ፋብሪካዎች ላይ ተግባራዊ እንደሚሆንና የሚገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ወደ ሌሎች ዘርፎችም እንዲሰፋ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ የፋብሪካ ተረፈ ምርቶችን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ለዘላቂ የኬሚካል አያያዝ፣ ሃብትን በአግባቡ ለመጠቀም፣ የፋብሪካ ተረፈ ምርቶችን በአግባቡ ለማስወገድና እና የባለሙያዎችን አቅም ለማሳደግ የሚያግዝ መሆኑን የተናገሩት ደግሞ የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ስለሺ ለማ ናቸው።

የአካባቢ ደኅንነትን ማስጠበቅ የፕሮጀክቱ ዋነኛ ዓላማ ነው ያሉት አቶ ስለሺ፤ በመንግሥትና በልማት አጋሮች የተቀረፀው ፕሮጀክት አከባቢን የማይጎዳና ለኅብረተሰቡ ተስማሚ መሆኑን እንዲሁም የባለሃብቶችን የምርትና አገልግሎት ተወዳዳሪነት ለመጨምር፣ ወጪ ለመቆጠብ፣ ምርታማነትን ለማሳደግና አቅም ለመፍጠር መነደፉን አንስተዋል።

እንደ አቶ ስለሺ ገለጻ፤ በአሁን ወቅት ሀገራት ምርቶች ለመሸመት አካባቢና ሕዝብን ሳይጎዱ መመረታቸውን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ ምርቶች በየትኛውም የገበያ መዳረሻዎች የሚቀርቡ በመሆናቸው ብዛት ያለው ምርት በማምረት ለዓለም ገበያ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

የአፍሪካ ሰርኩላር ኢኮኖሚ ኔትወርክ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጠና አስተባባሪ ቤዛዊት እሼቱ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠርና የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት ረገድ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ዘርፉ ትልቅ ሚና እንዳለው አንስተው፤ ኔትወርኩ በፕሮጀክቱ አተገባበር ዙሪያ ለተቋሙ በሥልጠና መልክ የቴክኒክና መሰል ድጋፎችን እንደሚያደርግ አመልክተዋል።

እንደ አስተባባሪዋ ገለጻ፤ በዓለም ገበያዎች አከካባቢን በመጉዳትና ማኅበራዊ እሴትን ሳያማክሉ የሚመረቱ ምርቶች ተቀባይነት እያጡ በመሆኑ፣ ይህ ፕሮጀክት ብክነትንና ብክለትን ባላስከተለ መልኩ በማምረት ኢትዮጵያ በዓለም ገበያዎች ተወዳዳሪ እንድትሆን ይረዳል፡፡



# ኢትዮጵያ ለቅድመ መደበኛ ትምህርት የሰጠችው ልዩ ትኩረት የብዙ ሀገራትን ትኩረት እየሳበ ነው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች መሆኗ የብዙ ሀገራትን ትኩረት እየሳበ ነው ሲሉ የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ኮራ ጡሹኔ ተናገሩ። የዑጋንዳ ከፍተኛ የትምህርት ፖሊሲ ባለሙያዎች በኢትዮጵያ በመገኘት በትምህርቱ ዘርፍ የልምድ ልውውጥ እያካሄዱ ነው።

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ኮራ ጡሹኔ(ዶ/ር) እንደገለጹት የልምድ ልውውጡ በዑጋንዳ መንግሥት በቀረበ ጥያቄ በኢትዮጵያ በትምህርቱ ዘርፍ እየተደረጉ ባሉ የለውጥ ሥራዎች ላይ ልምድ ለመቅሰም ያለመ ነው።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ ጉብኝቱ ኢትዮጵያ ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ባሉት ደረጃዎች የተደረጉትን የካሪኩለሞች አቀራረጽ፣ የይዘትና የትምህርት አሰጣጥ ለውጦች እና በትምህርት ጥራት በተለይም በፈተና አሰጣጥ ሂደት ላይ ያሉትን አሠራሮች በመመልከት ልምድ ለመውሰድ የተደረገ ነው።

እያንዳንዱ ሀገር የራሱ የሆነ ምርጥ ተሞክሮ አለው የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታው ከልምድ ልውውጡ ኢትዮጵያም ከዑጋንዳ የምትወስዳቸው መልካም ተሞክሮዎች ይኖራሉ ብለዋል።

በኢትዮጵያ የትምህርት አሰጣጡ ላይ የይዘት ለውጦች መደረጋቸውንና ከንድፈ ሀሳብ ባለፈ ትምህርት አሰጣጡ በተግባር ላይ አተኩሮ በጥራት እንዲሰጥ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው ጥራት በአንዴ የሚመጣ ነገር ባይሆንም ጅማሮዎቹ ጥሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የመምህራን ልማት ላይም ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመው በመጪው ክረምት በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ 50ሺ መምህራን ሥልጠና እንደሚገቡ አመላክተዋል። በዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩ መምህራንም በድህረ ምረቃ፣ በማስተማር ሥነ ዘዴ እና የተለያዩ ሥልጠናዎች እንዲወስዱ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አብራርተዋል።

የዑጋንዳ የትምህርት ፖሊሲ ማሻሻያ ምክትል ኮሚሽነር ጆሴፍ ሙቫዋላ(ዶ/ር) በበኩላቸው መንግሥት የትምህርት ጥራቱን ለማሻሻል ያለውን ቁርጠኝነት አድንቀው ዑጋንዳ ከዚህ ልምድ ትማራለች ብለዋል። በዩኒቨርሲቲ ማጠናቀቂያ እየተሰጠ ያለው የመውጫ ፈተናም ትልቅ ልምድ የሚወሰድበት መሆኑን አክለው ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ በትምህርቱ ዘርፍ ያሉትን መልካም ነገሮች በሙሉ ዑጋንዳ ልምድ ወስዳ ትተገብራለች ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ በቀጣይም ከኢትዮጵያ ጋር በዘርፉ በጋራ በመሥራት መልካም አፍሪካውያን እናፈራለን ብለዋል።

አብዛኛው ሀገራት የትምህርት ፖሊሲዎችን ሳያሻሽሉ ለረጅም ዓመታት ይቆያሉ ያሉት ኮሚሽነሩ ፖሊሲዎችን በየጊዜው በማሻሻል የሚፈጠሩ ስህተቶችን ማረም ያስፈልጋል ብለዋል።

ልዑካኑ በቆይታቸው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን፣ ኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲን እንዲሁም የተመረጡ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ምልከታ የሚያደርጉ ሲሆን በአዲስ አበባ ያሉ የቱሪዝም መስሕቦችን በተለይም የዓድዋ ሙዚየምን ይጎበኛሉ ተብሏል።

# የትብብር ማዕቀፉ መፈረም የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት የውሃ ሀብታቸውን በፍትሐዊነት እንዲጠቀሙ ዕድል ይፈጥራል

**ሞገስ ፀጋዬ**




አዲስ አበባ፡- የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማዕቀፉን አፅድቀው የናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ ኮሚሽን ከተቋቋመ የውሃ ሀብታቸውን በፍትሐዊነት ለመጠቀም እድል እንደሚፈጥር የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ ባለፉት 25 ዓመታት የሠራቸው ሥራዎችና በአባል ሀገራት መካከል እንዴት ተጠቃሚነትን ማሳደግ ይቻላል በሚለው ሀሳብ ዙሪያ የባለድርሻ አካላት ውይይት ትናንት ተካሂዷል።

በውይይቱ ወቅት ንግግር ያደረጉት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታ አብርሃ አዱኛ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ መሥራችና የዓባይ ተፋሰስ (የናይል ቤዚን) ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ የትብብር ማዕቀፉን ስምምነት (CFA) የመጀመሪያ ፈራሚና በፓርላማ ያፀደቀች ሀገር ናት።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ ኮሚሽንን ለማቋቋምና የጋራ የውሃ ሀብትን በጋራ ለመጠቀም የተፋሰሱ አራት ሀገራት የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱን አፅድቀዋል። በቀሪዎቹ የተፋሰሱ ሀገራት የትብብር ማዕቀፉ ከተፈረመ አባል ሀገራት የውሃ ሀብታቸውን በጋራ ለመጠቀም ዕድል ይፈጥራል ።

እንደ ሀገር ለናይል ቤዚን መጠቀም ባለብን ልክ አልተጠቀምንም ያሉት አብርሃ (ዶ/ር)፤ ወደፊት በትክክል ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ፈጥረናል። የተፈጠረው መደላድል የትብብር ማዕቀፉ ስምምነት እንዲፈረምና የናይል ቤዚን ኮሚሽን ሲቋቋም ሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት የውሃ ሀብትን በትክክል እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በዓባይ ተፋሰሶች ዜጎችን በማስተባበር የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች እየሠራች መሆኑን ገልጸው፤ ይህም በታችኛው የተፋሰሱ ሀገሮች ሊኖር የሚችለውን የውሃ ሀብት አጠቃቀም የሚያስተካክልና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል።

ነገር ግን የጋራ ኮሚሽን በማቋቋም ውሃን የመጠቀም መብትን በጋራ ማስከበር እንደሚገባ ገልጸዋል።

እንደ አብርሃ (ዶ/ር) ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ከናይል ቤዚን ተጠቃሚ መሆን አለባት። የናይል ቤዚን ባስቀመጠው የአስር ዓመት እቅድ መሠረት በኃይል፣ በምግብ ዋስትና፣ በአየር ንብረት ለውጥ እና በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አጠቃቀም ዙሪያ ዕቅድ ይዛ መጠቀም ያለባትን እየተጠቀመች ነው። ለአብነትም በአማራ ክልል መገጭና ጣና በለስ የመስኖ ልማትን ለማልማት የተጀመሩ ሥራዎች አሉ።

የኃይል ንግድን በተመለከተም ከተፋሰሱ አባል ሀገራት ጋር የጋራ ልማት እንዲኖር በኢትዮ-ሱዳንና በኢትዮ-ደቡብ ሱዳን የተጀመሩ ሥራዎች መኖራቸውን ገልጸዋል።

የናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ ዋና ዳይሬክተር ፍሎረንስ ግሬስ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ ወደ ታሰበለት ኮሚሽንነት እንዲሸጋገር የናይል ተፋሰስ ሀገራት ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው። የናይል ቤዝን ኢንሼቲቭን (NBI) ወደ ኮሚሽንነት እንዲሸጋገር አባል ሀገራት የትብብር ማዕቀፉን (CFA) እንደ ብሔራዊ ሕግ ማፅደቅ ይጠበቅባቸዋል።

አሁን ላይ አራት ሀገራት ማፅደቃቸውን በመግለጽ፤ የትብብር ማዕቀፉን ያፀደቁ ሀገራትን ቁጥር ለማሳደግ እየተሠራ ነው። ኢትዮጵያ ቀድማ ማፅደቋንና ኮሚሽኑ እውን እንዲሆን ተገቢውን እገዛ እያደረገች ትገኛለች ብለዋል።

የናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ የተፋሰሱ ሀገራት የውሃ አጠቃቀም እንዲሻሻል እየሠራ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፣ የተፋሰሱ ሀገራት ዜጎች የኢኮኖሚ እድገት ፈተና ገጥሟቸዋል። እንዲሁም የምግብ ዋስትና ችግር፣ የልማት እድገትና የሕዝብ ቁጥር እድገት አለመመጣጠን ሌላው ችግር መሆኑን በመግለጽ፣ ችግሮችን ለመቅረፍ የተፋሰሱ ሀገራት የጋራ ሀብትን በጋራ እንዲያለሙና ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።


ወ/ሮ ሸዊት ሻንካ


አቶ ጀማል አባሶ

# አገልግሎቱ የትራፊክ አደጋ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት መሥራት ይጠበቅበታል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የመንገድ ደኅንነት እና መድን ፈቃድ አገልግሎት የትራፊክ አደጋ ላይ መሠረታዊ ለውጥ እንዲመጣ መሥራት እንዳለበት የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የመንገድ ደኅንነት እና መድን ፈቃድ አገልግሎት የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር እቅድ አፈፃፀም በትላንትናው እለት ገምግሟል።

በግምገማው የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥና የተሽከርካሪ ምርመራ ላይ ያለው አሠራር ክፍተት እንዳለበት የተነሳ ሲሆን የተቋሙ የለውጥ ሥራዎች አፈፃፀም በሚመለከት አደረጃጀቱን መሠረት ባደረገ መልኩ ሪፖርት አለማድረግ እና ሪፖርቶች ወቅታዊ የመረጃ ፍሰትና የመረጃ ተዓማኒነት የሌላቸው መሆኑ ተነስቷል።

በወቅቱ የቋሚ ኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ እንደገለጹት፤ በሃገራችን በመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚከሰተው ሞት፣ የአካል ጉዳትን እና የንብረት ውድመት ቀላል የሚባል አይደለም። በዚህም አገልግሎቱ የትራፊክ አደጋ ላይ መሠረታዊ ውጤት እንዲመጣ መሥራት ይኖርበታል ብለዋል።

ሰብሳቢዋ፤ አገልግሎቱ አሁን እየተገበረው ያለው የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አመኔታ የጎደለውና የተዝረከረከ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይ የመረጃ ሥርዓቱን ለማዘመን እየተሠራ ያለው ሥራ እንዲፋጠንና ውጤት እንዲመጣ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት ይኖርበታል ሲሉ ጠቁመዋል።

በአፈጻጸም ሪፖርቱ የቀረበው የአገልግሎት እርካታ ቁጥር የተጋነነ መሆኑን የገለጹት ሰብሳቢዋ፤ አገልግሎቱ የአገልግሎት እርካታ በውስን ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ተግባራት መሆን ይኖርበታል ብለዋል።

አገልግሎቱ የተለያዩ ሁነቶችን በማዘጋጀት ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተጀመረው አሠራር የሚበረታታ በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም ተናግረዋል።

የአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጀማል አባሶ በበኩላቸው፤ የመንጃ ፍቃድ አሰጣጡን ለመቆጣጠር በክልል ደረጃ አቅጣጫ በማስቀመጥ እርምጃ እየተወሰደ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ በዚህም የተሽከርካሪ ምርመራ ሲካሄድም በኦንላይን መከታተል የሚያስችል ሶፍትዌር ከኢትዮ- ቴሌኮም ጋር በመሆን የማበልፀግ ሂደት ላይ ነው ብለዋል።

አገልግሎቱ መረጃዎችን በአግባቡ መመዝገብ የሚያስችለውን የዲጂታላይዜሽን ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ በቅርቡ ወደ ተግባር የሚገባ ይሆናል ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ ፤ የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ ተቋሙ የተለያዩ ሥራዎችን አከናውኗል። በዚህም በስድስት ወራት በትራፊክ አደጋ የሞተው የሰው ቁጥር አንድ ሺህ 358 ነው። ይህም ከአምናው ጋር ሲነጻጸር የ514 ልዩነት አለው። ይህም የተሠሩ ሥራዎች ውጤት ማሳያ ነው ብለዋል።

እንደ ሀገር ዘጠኝ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ተሽከርካሪዎች ላይ የቁጥጥር ሥራ ተሠርቷል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ በሀገሪቱ ካለው የመኪና ቁጥር ጋር ሲነጻጸርም በአንድ ተሽከርካሪ በአማካይ ከአምስት ጊዜ በላይ ቁጥጥር ተደርጓል ብለዋል።

ቁጥጥር ከተደረገባቸው ተሽከርካሪዎች መካከል ሁለት ነጥብ 17 ሚሊዮኑ ላይ እርምጃ ተወስዷል። በዚህም አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ለመንግሥት ገቢ ሆኗል ሲሉ አብራርተዋል።

በዋናነት ከሚጠቀሱት የሕግ ጥሰቶች መካከል ትልቁን ቁጥር የሚይዙት የደኅንነት ቀበቶ አለማሰር፣ ትርፍ መጫን እና ቴክኒክ ጉድለቶች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

# አዲስ አበባ

## ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ8 ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን አስተናግዳለች

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከስምንት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን በማስተናድ 49 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በኢኮኖሚው ላይ ፈሰስ መደረጉን የከተማዋ ባሕል፣ ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ።

የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሣው (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሁን ላይ የከተማዋ የቱሪዝሙ እንቅስቃሴ የተሻለ እና በጥሩ ደረጃ ላይ ነው።

በከተማዋ የተገነቡት አዳዲስ ፕሮጀክቶች የከተማዋን የቱሪስት ቁጥር በእጅጉ እንዲጨምር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረጋቸውን የተናሩት ቢሮ ኃላፊዋ፤ በዚህም ባለው ቀመር ስምንት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ከተማዋን መጎብኘታቸውን ተናግረዋል።

በዘጠኝ ወር ውስጥ ከታቀደው በላይ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ከተማዋን መጎብኘታቸውን የተናገሩት ኃላፊዋ፤ በገቢ ደረጃም በፊት በነበረው ዝቅተኛ ቀመር ተሰልቶ 49 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በጎብኚዎቹ አማካኝነት በተለያየ መልኩ ኢኮኖሚው ላይ ፈሰስ መሆኑን ተናግረዋል።

አዲስ አበባ ከፍተኛ የሀገር ውስጥ የቱሪስት እንቅስቃሴ ያለባት ከተማ ናት ያሉት ቢሮ ኃላፊዋ፤ ሀገሩን ለማወቅ ከሚመጣው ቱሪስት አንጻር በተለይ ከዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ምርቃት በኋላ የመጣው የቱሪስት ቁጥር እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

አዲስ አበባ የዲፕሎማቲክ ተቋማት መቀመጫ እንደመሆኗ ከሱዳን፣ ከሶማሌ፣ ከጅቡቲ፣ ከኤርትራ እና ከተለያዩ ጎረቤት ሀገራት ለሕክምና እና ለቢዝነስ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ወደ መዲናዋ እንደሚመጡ ጠቁመዋል። በመጀመሪያው ስድስት ወር ውስጥ 465 ሺ 366 የውጭ ሀገር ጎብኚዎች አዲስ አበባን መጎብኘታቸውንም ገልፀዋል። በዚህም 29 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር በተለያየ መልኩ ከጎብኚዎቹ መገኘቱንና ኢኮኖሚው ላይ ፈሰስ መደረጉን አስረድተዋል።

ከተማዋ በተገነቡ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ተመራጭነቷ እያደገ መምጣቱን የሚናገሩት ዶክተር ሂሩት ካሣው፤ ሁሉም በከተማዋ የሚገኙት አዳዲስ መስሕቦች ለውጭ ሀገር እና ለሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ምቹ እና ሳቢ መሆናቸውን ገልጸዋል።


ሂሩት ካሣው (ዶክተር)

ቱሪስቶች መጥተው የሚስተናገዱባቸው ሆቴሎች እንዲሁም የከተማዋ መንገዶች ምቹ ማድረግ ወሳኝ በመሆኑ በከተማዋ እየተገነቡ ያሉት የኮሪደር ልማት ሥራዎች ሲጠናቀቁ ለቱሪዝሙ ዘርፍ ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳላቸው ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊዋ ገለፃ፤ የቱሪስት ከተሞች በጨለማ ጭምር ሰው የሚዝናናባቸውና በቂ ብርሃን ያላቸው ናቸው። የኮሪደር ልማቱ ሥራ ሲጠናቀቅ መንገዶች ለእግረኞች ምቹ ስለሚሆኑ ጎብኚዎች በእግር ጉዞ ከተማዋን የሚጎበኙበት ዕድል ይፈጥርላቸዋል። አጠቃላይ በአዲስ አበባ የሚሠራው የልማት ሥራ ከተማዋ የቱሪዝምን መስፈርት የምታሟላ ምቹ ከተማ እንድትሆን የሚያስችላት ነው።

# በሸገር ከተማ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለ115 ሺ ወጣቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**አስቴር ኤልያስ**

ሸገር፡- በሸገር ከተማ በተያዘው በጀት ዓመት ዘጠኝ ወር ጊዜ ውስጥ ለ115 ሺ ሥራ አጥ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የከተማው ምክትል ከንቲባ አቶ ጉዮ ገልገሎ አስታወቁ።

ምክትል ከንቲባው ሰሞኑን በሸገር ከተማ እየተካሔደ ባለው የመስክ ምልከታ ላይ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት፤ የሸገር ከተማ የቀጣዩ ትውልድ ከተማ በሚል የሕዝብን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥያቄ ለመመለስ ሲባል በለውጡ መንግሥት ታቅዶ የተመሠረተ ሲሆን ከተማው አንዱ የትኩረት አቅጣጫው አድርጎ ሲሠራ የቆየው ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህም መሠረት በተያዘው በጀት ዓመት ወደ 140 ሺ የሥራ ዕድል ለመፍጠር አቅዶ በዘጠኝ ወር ውስጥ ለ115 ሺ ሥራ አጥ ወጣት የሥራ እድል መፍጠር ችሏል።

የሥራ ዕድል ፈጠራው የሚጀምረው ከሥልጠና ነው ያሉት ምክትል ከንቲባው፣ ሠልጥነው ከተደራጁ በኋላ መሥሪያ ቦታ የሚሆን ከ166 በላይ ሔክታር መሬት ተሰጥቷቸዋል ብለዋል። በቀጣይ ሌሎች ሼዶችም የሚያስፈልጉ በመሆናቸው በሕገ ወጥ መንገድ የተያዙ ሼዶችን በማስለቀቅና ሌሎችንም በመሥራት በጥቅሉ ወደ አንድ ሺ 200 ሼዶችን እንዳቀረቡላቸው ተናግረዋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ የሥራ ዕድሉ የተፈጠረላቸው ወጣቶች የብድር አቅርቦት ስለሚያስፈልጋቸው በዚያ



ፎቶ - በሀዱሽ አብርሀ

አቶ ጉዮ ገልገሎ

በኩል በስፋት ሲሠራበት ቆይቷል። ከብድር ጋር ተያይዞ እስካሁን በበጀት ዓመቱ ከታቀደው 400 ሚሊዮን ብር ውስጥ ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ ብድር ተመቻችቶላቸዋል።

አቶ ጉዮ፣ የሥራ አጡ ቁጥር ከፍ ያለ ነው ሲሉ ጠቅሰው፤ ይሁንና በበጀት ዓመቱ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የተደረገው እንቅስቃሴ የተሻለ ነው ብለዋል። እቅዱን በቀጣዮቹ ወራት በመሥራት ሙሉ ለሙሉ ስኬታማ ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሆኑም አስረድተዋል።

እንደ ምክትል ከንቲባው ገለጻ፤ መንግሥት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ያለው የግብርና ተነሳሽነት ላይ ነው። እነርሱም ሲሠሩበት የቆዩት አንዱ የግብርና ተነሳሽነት ላይ ነው። ለዚህም ስኬታማነት ከአንድ ሺ 900 በላይ ክላስተሮችን እና ከሦስት ሺ 800 በላይ ሼዶችን ገንብተው ሙሉ በሙሉ ለወጣቶች ሰጥተዋል። አብዛኞቹ ተጠቃሚዎች የአርሶ አደሩ ልጆች ሲሆኑ፣ ሌሎችም ወጣቶች ተካትተውበታል።

በሥራ ዕድል ፈጠራው ላይ ሕዝቡ እያሳየ ያለው ተሳትፎ አበረታች ነው ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ ሕዝቡ በሚሠራቸው በእያንዳንዱ የልማት ሥራዎች ከጎናችን በመሆን እያገዘን ነው። ክላስተሮቹና ሼዶቹ የተሠሩትም በሕዝብ ተሳትፎም ጭምር ነው። በልማቱም ሆነ በፀጥታ ሥራው ላይ ተባባሪነቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ልቆ የታየበት ነው። እያደረገ ባለውና በሚያደርገውም ድጋፍ ምስጋና በማቅረብ ነገ ለሚደረገው የብልፅግና ጉዞም ከጎናቸው እንዲሆኑ ጥሪ እናቀርባለን ብለዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የሥራ ዕድል ፈጠራ ቢሮ በጋራ በመሆን በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ያተኮረ የመስክ ምልከታን ለጋዜጠኞች እያስጎበኙ ይገኛሉ።

# የውሃና ኢነርጂ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እያገኙ መሆኑም ተገልጿል፡፡

ሚኒስቴሩ በዘርፉ ከተሠማሩ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ልማታዊ ድርጅቶች ጋር ትናንት ተወያይቷል፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ መንግሥት የውሃና ኢነርጂ ተደራሽነትን ለማሳደግ ለሚሠማሩ ለግልና ልማታዊ ድርጅቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

መንግስት የመጠጥ ውሃና የገጠር ኢነርጂን ተደራሽነት ለማሳደግ ከልማታዊ ድርጅቶች ጋር እየሠራ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የሰብዓዊ ጉዳዮች ድጋፍን ጨምሮ በመጠጥ ውሃና ኢነርጂን አቅርቦት በጋራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ዓለም ባንክ የመጠጥ ውሃና ኢነርጂ ተደራሽነት ላይ ድጋፍ እንደሚያደርግ ጠቅሰው፤ ዩኒሴፍም በልማታዊ ድርጅቶቹ በኩል ሰብዓዊ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ልማታዊ ድርጅቶች የመጠጥ ውሃና ኢነርጂ ተደራሽነትን ለማሳደግ እንደሚረዱ በመግለጽ፤ መንግሥት ከድርጅቶቹ ጋር የሀብት ብክነት ሳይኖር በጋራ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን አመላክተዋል።

የሀገሪቱ የመጠጥ ውሃና ኢነርጂ ሽፋን ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን ያነሱት ሚኒስትሩ፤ በተለይም ዓለም ባንክ፣ ዩኒሴፍ፣ የኔዘርላንድ፣ ዴንማርክ፣ ኤምባሲዎችን ጨምሮ የአፍሪካ ልማት ባንክና የተለያዩ የልማት ድርጅቶች አጋር መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

በአንዳንድ ልማታዊ ድርጅቶች የሚስተዋለውን ችግር ለመቅረፍ ክትትል በማድረግ ላይ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የልማታዊ ድርጅቶች ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በከርሰ ምድር ውሃ ላይ ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሀብቶች መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ያሉት ኢንጂነር ሀብታሙ፤ በሪል ስቴቶች፣ ሆቴልና ሪዞርት የተሰማሩ ባለሀብቶች የጉድጓድ ውሃን ቆፍረው ለማኅበረሰቡ እንዲያቀርቡ ማበረታቻ ይደረግላቸዋል ብለዋል፡፡

የጉድጓድ ውሃን ለማውጣት የሚጠቅሙ ማሽኖች ላይ ባለሀብቶች ሊሳተፉ እንደሚገባቸው ጠቅሰው፤ ባለሀብቶች ፍቃድ አውጥተው በዘርፉ ሊሠማሩ እንደሚችሉ አመላክተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ከ71 ሚሊዮን ዜጎች ንጹሕ መጠጥ ውሃ እያገኙ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህም በአማካኝ 68 በመቶ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ግጭት ባለባቸው፣ ድርቅና የተፈጥሮ አደጋ ችግር ያለባቸው አካባቢዎችን መልሰው እንዲያገግሙ የማድረግ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በተለይም አማራ ክልል፣ ትግራይ፣ የተወሰኑ የኦሮሚያ አካባቢዎች ላይ እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

የኢነርጂ አቅርቦትን ለማሳደግ ሰዎች በአካባቢያቸው ላይ ኃይል ማግኘት የሚችሉበትን አማራጮች እየቀረቡ እንደሚገኙ በመግለጽ፤ በተለይም የፀሐይ ኃይል አቅርቦት፣ ባዮጋዝ፣ ኃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሰሠራ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

# ክልሉ ከሮዝመሪና በርበሬ ምርቶች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የግብርና ምርቶችን ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ በስፋት በማምረትና ወደ ተለያዩ ሃገራት በመላክ ለሃገር የውጭ ምንዛሪ ግኝት የበኩሉን ሚና ለመጫወት እየተረባረበ ይገኛል። ከእነዚህም የግብርና ምርቶች መካከል በርበሬና ሮዝመሪ ዋነኞቹ ሲሆኑ በተለይም በርበሬ ላይ እሴት በመጨመርና በማቀነባበር በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው።

‹‹ቀደም ሲል ቡና እና ቅመማ ቅመም በዚህ ክልል እምብዛም አይታወቅም ነበር›› ያሉት አቶ ዑስማን፤ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ግን የቅመማ ቅመምንም ሆነ የቡና መሬትን ሽፋን የማስፋፋት እንዲሁም ምርታማነቱን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል። በዚህ ዓመት ወደ 52 ሚሊዮን የቡና ችግኝ ለመትከል ርብርብ እየተደረገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 10 ሚሊዮኑ ከሚያዚያ ጀምሮ እየተተከለ መሆኑን ጠቁመዋል።

በቅመማ ቅመም ልማት ረገድም በክልሉ ያለውን ምቹ የአየር ንብረት በመጠቀም ዝንጅብል፣ ኮሰረት፣ ድንብላልና ሮዝመሪ ወደ ማምረት መገባቱንም ተናግረዋል። ‹‹በተለይ ሮዝመሪ ላይ ከፍ ባለመንገድ በማምረት ለውጭ ገበያ በስፋት ለማቅረብ ጥረት እያደረግን ነው›› ያሉት አቶ ዑስማን፣ በዚህ መነሻ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከስልጤ ዞን ብቻ 22 ሺ 760 ኩንታል ሮዝመሪ ወደ ተለያዩ የዓለም ሃገራት ልከን 4 ነጥብ 1 ሚሊዮን ዶላር ማስገባት ችለናል ሲሉ ጠቁመዋል።

‹‹በአካባቢው ሮዝመሪ ከዚህ በፊት የሚታወቀው ለመጥበሻነት እንጂ ዶላር ማምጫነት አይደለም፤ አሁን ሮዝመሪ ከመጥበሻ ወጥታ ወደ ዶላር ማምጫና ሥራ ዕድል መፍጠሪያ የሃገር ሃብት ምንጭ ሆናለች›› ብለዋል።

አክለውም ‹‹የእኛ ሮዝመሪ አሁን ላይ አውሮፓ ገበያ ገብቶ ግሎባል ካፕ ሰርተፊኬት አግኝቷል። ሦስት ሺ አርሶአደሮች ግሎባል ካፕ ሰርተፍኬት እንዲያገኙ አድርጓል›› ያሉት አቶ ዑስማን፣ አርሶአደሮቹ ይህንን ሰርተፍኬት ማግኘታቸው ፕሪሚየም ፕራይዝ እንዲያገኙና አስተማማኝ ገበያ እንዲኖራቸው የሚያደርግ መሆኑን አብራርተዋል።

በመሆኑም የክልሉ መንግሥት ጥራቱን ጠብቆ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማምረትና ማስፋፋት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አመልክተዋል። ‹‹ሲጀመር አንድ ቀበሌ ላይ ነው የነበረው፤ አሁን መላው ስልጤ ወረዳዎች ላይ የማስፋፋት ሥራ ተሠርቷል። በትምህርት ቤቶች፣ በጤና እና በእምነት ተቋማት የመትከል ሥራ እየተሠራ ነው። ጉራጌ ላይ ወደ 2 ሺ ሄክታር አካባቢ ደርሷል›› ብለዋል።

ሥራው ወደ ሌሎችም የክልሉ አካባቢዎች የማድረስ ሥራ እየተሠራ መሆኑንና በቀጣይ ሌሎችንም ቅመማ ቅመሞችንን ለመዓዛማ ዘይት የሚውሉና በትንሽ መሬት ሃብት የሚመነጭባቸውን በመለየትና በስፋት በማምረት ለሃገር የውጭ ምንዛሪ ግኝት ሁነኛ ምንጭ ለመሆን ጥረት የሚደረግ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የክልሉ መረጃ እንደሚያመላክተው፤ ሮዝመሪ ድርቅንና አሲዳማ አፈርን የመቋቋም አቅሙ ከፍተኛ ነው። ደረቃማ በሆነ መሬት ላይ ምርት በመስጠትም ይታወቃል። ወደ ሕንድ፣ ዱባይ፣ መካከለኛው ምሥራቅና አውሮፓ ገበያ ከተላከው በርበሬ 90 በመቶ የሚሆነው ከስልጤ ዞን ቀሪው ከሃላባ ዞን ነው የተገኘው፤ ሮዝመሪው ግን ሙሉ ለሙሉ የተመረተው በስልጤ ዞን ነው።

# ምክክር - የዘላቂ ሠላም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ኮሚሽን ተቋቁሞም ወደ ሥራ ገብቷል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም በሀገሪቱ ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍን ከማን ምን ይጠበቃል? በተለይ ችግሮቻችንን በሠላማዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኙ ከማድረግ አንጻር ምን መሥራት አለበት? በሚለው ላይ የባለድርሻ አካላትን አስተያየት ጠይቋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ፃድቁ አብዶ እንደሚሉት፤ እንደ ሀገር ሠላምን ለማጽናት ከቤተሰብ ጀምሮ የሁላችንንም ርብርብና መልካም ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው። በተለይ መንግሥት ሠላምን ማረጋገጥ ተቀዳሚ ተግባሩ እንደመሆኑ ችግሮችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት በሆደሰፊነት መንቀሳቀስ አለበት።

መብቴ ተነክቷል፤ ጥቅሜ አልተረጋገጠልኝም የሚል ቅሬታ ያለው አካልም ሁሉም ችግሮች መፍትሔ ማግኘት የሚገባቸው በምክክርና ውይይት መሆን እንዳለበት አምኖ የሌሎችን ሀሳብ ለማዳመጥ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል።

ጥቅማችንን ለማረጋገጥ የምናደርገው እንቅስቃሴም ሠላማዊ ወገኖቻችንን ችግር ውስጥ የሚጥል እንዳይሆን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ።

በሁሉም ሃይማኖቶች አስተምሕሮ ውስጥ ወርቃማው ሕግ የሚባል እሳቤ መኖሩን የሚጠቅሱት ፓስተር ፃድቁ፤ ይህም ላንተ እንዲደረግልህ የምትፈልገውን ነገር ለሌላው አድርግ፣ አንተ ላይ እንዲደረግ የማትፈልገውንም በሌላው ላይ አታድርግ የሚል ነው።

ይህን ሕግ አክብሮ መንቀሳቀስ ችግሮችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት እንቅፋት የሚሆኑ ተግዳሮቶችን ሁሉ መሻገር ያስችላል።

ሠላምን በተወሰኑ አካላት ጥረት ብቻ ለማረጋገጥ መሞከር በአንድ እጅ እንደማጨብጨብ የሚቆጠር መሆኑን የሚገልጹት ፕሬዚዳንቱ፤ መንግሥት፣ የፖለቲካ ተዋናዮች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ሕዝቡና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ለሠላም መስፈን የየድርሻቸውን ጠጠር መጣል ይጠበቅባቸዋል።

በተለይ የሃይማኖት ተቋማት ተከታዮቻቸውን ሁሉ ለሠላም ዘብ እንዲቆሙ ማስተማር እንዳለባቸው የሚጠቅሱት ፓስተር ፃድቁ፤ አስተማሪዎች ነን የምንል የሃይማኖቱ ሰዎችም የምናስተምረውን ትምህርት በሕይወት በመግለጥ ለተከታዮቻችን አርዓያ ልንሆን ይገባል።

ለችግር መፈጠር ጥቂት ሰዎች አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ ሁሉ እያንዳንዳችን የምናደርገው እንቅስቃሴ ለሠላም መጥፋትም ለሠላም መስፈንም አስተዋፅዖ እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል የሚሉት ፓስተሩ፤ በኃይል መፍትሔ ለማምጣት የሚደረጉ ጥረቶች በሕዝቡ ላይ ጉዳት ከማስከተል ያለፈ ውጤት አያመጡም ብለዋል።

በመሆኑም አንዳችን በሌላችን ቦታ ሆነን ሌሎችን ማዳመጥ እና በምክክርና ውይይት ለችግሮች መፍትሔ ለማበጀት ቁርጠኛ መሆን ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባል መብራቱ ዓለሙ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጠሩ አለመረጋጋትና ግጭቶች በሰው ሕይወት፣ የንብረት ውድመት፣ መፈናቀልና ሰብዓዊ ቀውሶችን እያስከተሉ ነው። እነዚህን ችግሮች መቅረፍ የሚቻለው አንዳችን ሌላችንን ማዳመጥ ስንችል ነው። ለዚህ ደግሞ አካታች የውይይትና ምክክር መድረኮችን መፍጠር ያስፈልጋል።

ዘላቂ ሠላም ለማስፈን የፖለቲካ ኃይሎች፣ ሲቪል ማኅበራት፣ የሃይማኖት ተቋማትና መንግሥት ንቁ ታሳታፊ እንዲሆኑ ይጠበቃል የሚሉት መብራቱ (ዶ/ር)፤ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ አሁን ላይ እየሠራ ያለውም ግጭትን ለማስቆምና በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለውን ማኅበራዊ መስተጋብር ለማጠናከር ነው ብለዋል።

ስለሆነም ወደየትኛውም ግጭት ከማምራታችን በፊት አሉኝ የምንላቸውን ጥያቄዎች ሁሉ ወደፊት ማምጣትና በሠላማዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኙ በቁርጠኝነት መታገል ያስፈልጋል።

ሌላኛው ለሠላም መረጋገጥ መፍትሔ ሊሆን የሚችለው የፖለቲካ ሪፎርም ማካሄድ ነው የሚሉት ፖለቲከኛው፤ በዚህም ከሕገ መንግሥቱ ጀምሮ ተቋማትን መፈተሽና የመፍትሔው አካል እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል ሲሉም አፅንዖት ሰጥተዋል።

በሀገሪቱ የሚስተዋሉ የታሪክ ቁርሾዎችን መፍታትና በሚፈጠሩ ግጭቶች ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ለንግግርና ውይይት ምቹ ሁኔታ መፍጠርም ይጠበቅብናል ይላሉ።

አጠቃላይ የፖለቲካ ሥርዓታችን ጤናማ እንዲሆን ለፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፣ ለማኅበራዊ አንቂዎችና ለመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች የመነጋገርና የመቻቻል ባሕላችንን በምን መልኩ ማሳደግ እንደሚቻል ግንዛቤ መፍጠር እንደሚገባ የሚጠቁሙት መብራቱ (ዶ/ር)፤ ሠላምን በተወሰኑ አካላት ፍላጎትና እንቅስቃሴ ብቻ ማረጋገጥ አይቻልም ሲሉም ተናግረዋል።

በመሆኑም ከመንግሥት ጀምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ሚና መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

እንደ አስተያየት ሰጪዎቹ ማብራሪያ፤ የትኛውም ጥያቄ መፍትሔ ማግኘት የሚችለው በሠላማዊ ውይይትና ምክክር ነው።

ሠላም የሚረጋገጠውም በጥቂት ወገኖች ፍላጎት ሳይሆን የሁሉም ባለድርሻዎች ትብብርና ጥረት ሲታከልበት ነው።

ስለሆነም ዘላቂ ሀገራዊ ሠላም ለማስፈን መንግሥት፣ የፖለቲካ ተዋናዮች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ሕዝቡና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በትብብር መሥራት ይኖርባቸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስመንግሥት የሠላም ጥሪ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይገባል!

የሰው ልጆች የተለያዩ ፍላጎቶች አሏቸው። እነዚህን ፍላጎቶቻቸውን ለማሳካትም በየራሳቸው መንገድ ሊጓዙ ይችላሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ፍላጎቶቻቸውም ሆኑ፣ የፍላጎት ማሳኪያ መንገዶች በሌሎች ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት አዎንታዊ አልያም አሉታዊ ጉዳዮች ስለመኖር አለመኖራቸው በወጉ ማጤን የተገባ ነው።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያውያን (እንደ ግለሰብ፣ ቡድን ብሎም እንደ ሕዝብ) በዘመናት ጉዞ ውስጥ የሚፈልጓቸውን ጉዳዮች ለማሳካት አያሌ ትግሎችን አድርገዋል፤ በርካታ ውጣ ውረዶችንም አልፈዋል። በዛፍ ጥላ ስር ቁጭ ብሎ ከመምከር፣ በጠብመንጃ አፈሙዝ እስከ መዋደቅ የደረሱ ስልቶችንም ተከትለዋል።

በዚህም ነፃነትና ሉዓላዊነታቸውን አስጠብቀው ኖረዋል፤ ጭቆናን አስወግደዋል፤ እኩልነትና ፍትሐዊነት እንዲሰፍን የድርሻቸውን ተወጥተዋል፤ ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ በወንድማማችነትና ብዝኃነት አብረው እንዲኖሩ፣ ኢትዮጵያም እንደ ሀገር ጸንታ እንድትኖር አስችለዋል።

ይሄን መሰሉ የወል ጥቅምና ፍላጎቶች የፈጠሩት የሕልውና መንገድ እና የመንገዱ መዳረሻ የሆነው አብሮነት እና ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከዚህ በተቃራኒው በ“እኔ” እና “እኛ” ብቻ እሳቤ ላይ የተመሠረተ ያልተገባ አካሄድ ሕዝብንም ሀገርንም ዋጋ እያስከፈለ የዘለቀ ሐቅ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባውም።

በዚህ ረገድ ግለሰቦች አልያም ቡድኖች፤ ግለሰባዊ እና ቡድናዊ ጥቅምና ፍላጎትን ማዕከል በማድረግ አለመግባባትን፤ መገፋፋትን፣ አለፍ ሲልም ግጭትና ጦርነትን እየቀሰቀሱ ያልተገባ ሰብዓዊም ቁሳዊም ዋጋን ሲያስከፍሉ ኖረዋል።

“ትግል” የሚል የዳቦ ስም የሚሰጠው ይሄን መሰሉ ግለሰባዊ ብሎም ቡድናዊ ጥቅምን ብቻ ማዕከል ያደረገው ስልተ መንገድ፤ የትግልን ዓላማ እና ግብ ባልተረዳ መልኩ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፣ ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ ከፍ ያለ ቀውስ እና ያለመረጋጋት ውስጥ እንዲገቡ፤ ሰብዓዊም ሆነ ቁሳዊ ኪሳራንም ሳይፈልጉ እንዲያስተናግዱ እያደረገ ዛሬም ድረስ ዘልቋል።

ይሁን እንጂ የትግል ዓላማ ሕዝብን እንደ ሕዝብ ችግር ውስጥ የሚከትት፣ ሀገርንም እንደ ሀገር የሕልውና ስጋት የሚፈጥር ጉዳይ ሲገጥም፤ ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም ቢባል ያንን ችግርና አደጋ ለመቀልበስ ዜጎች ዋጋ ለመክፈል ወስነው የሚከተሉት አካሄድ ነው። ይሁን እንጂ ላለፉት አምስት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ አስርተ ዓመታት እየሆነ ያለው ግን ከዚህ እውነት ያፈነገጠ ነው።

ምክንያቱም፣ ነፃነቱ በተከበረለት ማኅበረሰብ ውስጥ ሆኖ በነፃ አውጪ ስም ተደራጅቶ ነፃውን ሕዝብ ነፃነት የማሳጣት አካሄዶች ተበራክተው ታይተዋል። ልማትና ማኅበራዊ ክብሩ በተጠበቀለት ማኅበረሰብ ውስጥ ሆነው፤ የማኅበራዊ ደኅንነት ዋስትና አረጋጋጭ ኃይል ሆነው በመከሰት ሕዝቡን ላልተገባ ማኅበራዊም፣ ኢኮኖሚያውም፣ ሥነልቦናዊም ቀውስ ሲዳረጉ ማየት እየተለመደ መጥቷል።

በእነዚህና መሰል ጉዳዮች እንደ “መታገያ” አጀንዳ በመያዝ በተለይ ደግሞ ከ2010ሩ ለውጥ ማግስት አያሌ ቡድኖች ራሳቸውን የሕዝብ ሕልውና አስጠባቂ አድርገው ስለዋል። በዚህም ሕዝብ እና መንግሥት መካከል አለመተማመን እንዲፈጠር፤ ይልቁንም ሕዝብ በደኅንነት ስጋት ውስጥ እንዲገባ እና መንግሥትም ከልማት ይልቅ ሠላምን ማስከበር ዋነኛ አጀንዳው እንዲሆን የማድረግ ተግባር ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ።

በርካታ ግጭቶችን ፈጥረዋል፤ ከፍ ያለ ዋጋ ያስከፈለ ጦርነትም ተከናውኗል። ዛሬም ይሄው በእነዚህ ቡድኖች ዘዋሪነት የሚከወን የግጭት አዙሪት ከማኅበረሰቡ ላይ እንዳይወርድ አድርገዋል። በአማራ፣ ኦሮሚያ እና በሌሎችም አካባቢዎች እየሆነ ያለውም ይሄው ነው።

መንግሥት ዛሬም ችግሮችን እነሱ ባነሱት የጠብመንጃ አፈሙዝ ብቻ ለመፍታት መሞከሩ ዘላቂ መፍትሔ እንደማይሆን በማመን ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ጥያቄ አለን ከሚሉ ነፍጥ አንሺዎች ጋር ለመነጋገር ተደጋጋሚ የሠላም ጥሪዎችን እያደረገ ይገኛል። በዚህ ጥሪቱም የተወሰኑት ተቀብለው ወደ መፍትሔ ሲሄዱ፤ አንዳንዶቹ ግን ዛሬም በጫካ ሆነው ነፍጥን እንደ መፍትሔ ቆጥረው ይገኛሉ።

ሆኖም በጠብመንጃ አፈሙዝ የሚካሄድ ትግልም ሆነ እንዲመለስ የሚፈለግ ጥያቄ፣ በውይይትና ድርድር ከሚገኘው በፍጹም የተሻለ አይደለም። ይልቁንም የትግል ዓላማው ለሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ ለማስገኘት፤ የሀገርንም ሕልውና ለማጽናት ከሆነ፤ ምርጫ ሊሆን የሚገባው ቁጭ ብሎ በሠላማዊ መንገድ መነጋገርና መፍትሔ ማምጣት ነው።

ምክንያቱም በሠላም መነጋገር የዜጎችን ሞትና መፈናቀል እንዲሁም ሰብዓዊ ቀውስን ያስቀራል። በአንጻሩ ጦርነት፣ ንብረት ያወድማል፣ አካል ያጎድላል፣ ክቡሩን የሰው ሕይወትም ይበላል፤ ከፍ ያለ ማኅበራዊና ሥነልቡናዊ ቀውስንም ያስከትላል። ይሄን የሚፈልግ የሕዝብ ጥያቄ አንጋቢ ኃይል ደግሞ ሊኖር አይችልም፤ አይገባምም።

ምክንያቱም ከጦርነት የሚያተርፈው የሀገር እና የሕዝብ ጠላት እንጂ፤ የሕዝብ ልጅና ሀገር አይደሉምና። መንግሥትም እንደ መንግሥት ለእነዚህ ኃይሎች ተደጋጋሚ የሠላም ጥሪ የሚያቀርበው የሚሄዱበት ያልተገባ አካሄድ ተገንዝበው ወደሠላሙ መንገድ ይመለሳሉ በሚል እሳቤ ነው።

በመሆኑም ጠብመንጃ አንግተው በጫካ ሆነው የሚዋጉ ሁሉ፤ ጫካ የመግባታቸው ምክንያት፣ ጠብመንጃ የማንሳታቸው ጉዳይ የሕዝብ ጥያቄ ከሆነ፤ የሕዝብ ጥያቄ የሚመለሰው በጦርነት ውስጥ ሕዝብን ዋጋ እያስከፈሉ ሳይሆን፤ በሠላም ቁጭ ብሎ በመነጋገር እና ከራስ ጥቅም ይልቅ የሕዝብን ጥቅምን በማስቀደም መሆኑን በመገንዘብ፤ በመንግሥት ለሚቀርቡ ተደጋጋሚ የሠላም ጥሪዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።።

## ሕዝብን ዕረፍት የሚነሱ የጥፋት ተግባራት ሲቆሙ ይገባል

ፌኔት (ከመሳለሚያ)

ኢትዮጵያን አላላውስ ብለው እግር እና እጇን ቀፍድደው ካሰሯት ጉዳዮች መካከል ልዩ ልዩ ጥቅሞችን እያሰቡ በተለያየ አቅጣጫ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ተግባር ዋነኛው ነው። እነዚህ ኃይሎች በተለያየ አቅጣጫ የራሳቸውን ብቻ ጥቅም አስበው የሚንቀሳቀሱ ስግብግቦች ናቸው። እነዚህ ብቻ አይደሉም፤ በሌላ በኩል ማመዛዘን ባለመቻል፤ «እኔ ብቻ ተወዳጅ፣ እኔ ብቻ ተደማጭ፣ እኔ ብቻ መሪ ልሁን» የሚሉም አሉ። እነዚህ ጉዶች ሕዝብን ዕረፍት እየነሱ፤ ኢትዮጵያዊነትን እያደበዘዙ ብዙዎችን ተስፋ እያስቆረጡ ነው።

ከሆዳቸው ውጪ የማይታያቸው ስግብግቦች፤ አገር ካልቆመች ማንም እንደማይቆም፤ እነርሱም ቢሆኑ የዘረፉትን መብላት እንደማይችሉ ለማወቅ እንኳ ጭንቅላታቸውን የማይጠቀሙበት ጭፍኖች መብዛታቸው ሀገርን በብዙ መልኩ ዋጋ እያስከፈላት ነው። በየአቅጣጫው በየጫካው ተደራጅተው፤ በቡድን ተሸሽገው መኪና እያስቆሙ የሚዘርፉ እና ሕዝብ የሚያሰቃዩ፤ አልፈው ተርፈው መኪና ከማቃጠል ባሻገር ልጆችን ያለአባት እና ያለእናት የሚያስቀሩ የሰውን ሕይወት የሚቀጥፉ ጥጋበኞች በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በሕዝብም እባካችሁ አቁሙ ቢባሉም ለመስማት ፈቃደኛ አልሆኑም።

ሕዝብ አያውቅም ማለት አይቻልም። ለጊዜው ቢሸፋፈንም መገለጡ አይቀርም። በየመንገዱ ከሚካሄደው ዘረፋ ባሻገር ሰው እያሰማሩ የሚያስገድሉ እና የሚገድሉም አሉ። ከላይ ከላይ በቡድን ተደራጅተው የዕለት ዘረፋ እና የዕለት ሆድ መሙያ አስፀያፊ ድርጊት የሚፈፅሙ ቢመስሉም፤ አሰማሪዎቹ ለውጪ ኃይል የተገዙ የኢትዮጵያ ጠላትን ፍላጎት የሚያስፈፅሙ ስለመሆናቸው አያጠራጥርም።

እነዚህ ተራ ሆነው በየቦታው መንገድ ዘርፈው ሀገር እና ሕዝብን የሚያሰቃዩትም ሆኑ፤ በውጪ ጠላቶች ተገዝተው ኢትዮጵያን የሚበድሉ እኩዮች ለጊዜው የተሳካላቸው ቢመስላቸውም በሕዝብ ታፍነው እንደሚጠፉ አያጠያይቅም።

በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ዘራፊ ቡድኖች በየመንገዱ ሕዝብ እያስጨነቁ፤ በሚፈፅሙት ንጥቂያ እና ዝርፊያ አሁን ላይ ሕዝብ እየተማረረ መሆኑን ማወቅ አለባቸው። የጊዜ ጉዳይ እንጂ የተዘረፈና የተበደለ ሕዝብ ዘራፊን ማጥፋቱ አይቀርም፤ ምክንያቱም ተዘራፊ ለጊዜው እንጂ ዘለዓለሙን ሲዘረፍ አይኖርም።

ሀገር ለማፍረስ የተነሱና ሕዝብን ዕረፍት የሚነሱ ከድርጊታቸው ካልታቀቡ ሁኔታው አደገኛ ይሆናል። ይህ ሲባል ጦሱ በቀላሉ የሚታይ አለመሆኑን መገንዘብ ይገባል። በየቀኑ የሚፈፅሙት ድርጊት የሚዘረፈው ሰው ላይ እና የሚሞተው ሰው ቤተሰብ ላይ መጥፎ የጥላቻ መርፌን ብቻ ሳይሆን ሚስማር እየመቱ ነው። ሚስማሩ በበዛ ቁጥር ሰው እንጨት አይደለም፤ ሥጋ እና አጥንት በመሆኑ ቁስሉ ያመዋል። ቁስሉ አመርቅዞ አደጋ ከማስከተሉ በፊት አቁሳዮቹን ማስወገዱ አይቀርም።

መንግሥት ብቻውን ምንም ማድረግ አይችልም። ሕዝብ መተባበር አለበት። በአማራ ክልልም ሆነ በኦሮሚያ ክልል እንዲሁም በሌሎችም በአንዳንድ አካባቢዎች ሕዝብን እያማረሩ ያሉ የተለያዩ ቡድኖች አሉ። እነዚህ ቡድኖች አደብ ሊገዙ የሚችሉት ሕዝብና መንግሥት ሲተባበሩ ብቻ ነው።

በብሔርና በሃይማኖት ስም በየሰፈሩ የተለያዩ ቡድኖችን በነፃ አውጪ ስም በማደራጀት ኢትዮጵያን የማፍረስ ሴራ ዛሬ የተጀመረ አይደለም። ሆኖም በሠላም ወዳዱ ሕዝብ ጥረት ኢትዮጵያ ዛሬም አልፈረሰችም። ኢትዮጵያዊነት ሲጎላ እና ሕዝቡ በአንድ ላይ ለማደግ ሲጓጓ፤ በተቃራኒው ኢትዮጵያዊነትን ከመንደር አሳንሰው ማየት በሚፈልጉ አካላት ኢትዮጵያ በርካታ ገፈቶችን ስትቀምስ ቆይታለች። ዛሬም እየቀመሰች ነው። ከኢትዮጵያዊነት በላይ ብሔር እና ኃይማኖት መጉላት አለበት እያሉ ኢትዮጵያዊነትን ለመጥለፍ ገመድ ለሚጥሉት መሣሪያ ሆነው የሚያገለግሉ ጥቅማቸውን የሚያሳድዱ ደግሞ ለጊዜው ሕዝብን ዕረፍት ቢነሱም ቆይተው መጋለጣቸው እና በፍርድ አደባባይ መቆማቸው አይቀርም።

**በብሔርና በሃይማኖት ስም በየሰፈሩ የተለያዩ ቡድኖችን በነፃ አውጪ ስም በማደራጀት ኢትዮጵያን የማፍረስ ሴራ ዛሬ የተጀመረ አይደለም። ሆኖም በሠላም ወዳዱ ሕዝብ ጥረት ኢትዮጵያ ዛሬም አልፈረሰችም**

የሰው ልጅ በአፉ እያወራ በጭንቅላቱ ምን እንደሚያስብ አይታወቅም። ነገር ግን በየዋህነት ሴረኞችን እና ጥቅም አሳዳጆችን ቀርበው የሚከተሉ፤ የተነገረውን ሁሉ የሚያምኑ ደግሞ ብዙ ናቸው። ጉዳዩ ተራ በኪስ ስለሚገባ ገንዘብ አይደለም። እንደውም የሀገር ጥቅም ጉዳይ ብቻም አይደለም። እንደሀገር የመቆም አለመቆም ጉዳይ ነው። ስለሀገር ሲሉ ራሳቸውን የሰው ብዙ ናቸው። ለዚህ ነው፤ ሕዝብ አይን አፍጥጦ ጆሮውን አቁሞ የሚሰማው ጉዳይ የኢትዮጵያን አንድነት ጉዳይ ነው። ሕዝብ የሚፈልገው ኦሮሞ ከአማራው፣ አማራ ከትግሬው፣ ትግሬው ከአፋሩ፣ አፋር ከሱማሌው፣ ሱማሌ ከቤንሻንጉሉ፣ ቤንሻንጉል ከጋምቤላ፤ ጋምቤላ ከደቡቡ እና ሌሎቹም በአንድነት ሲኖሩ ማየት ነው። የኢትዮጵያ ትልቅነት ጉዳይ ሲነሳ ትኩስ እንባ በጉንጫቸው የሚያፈሱ ዜጎች የምናየውም ከዚሁ የሀገር ፍቅርና የአብሮነት ዕሳቤ አንጻር ነው።

የሕዝብን አንድነት ጉዳይ ለኢትዮጵያውያን የሞት የሽረት ጉዳይ ነው። የሕዝብ አንድነት መሸርሸር የሚያስከፍለው ዋጋ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን በእውቀት እጦት የታመሙ ጤነኛ መስለው መታመማቸውን ተረድተው ከመታከም እና ተገቢውን መድኃኒት በቅጡ ከመውሰድ ይልቅ በተለያዩ አካባቢዎች ቡድን አደራጅተው ሕዝብን ዕረፍት መንሳታቸውን ማቆምም ሆነ ማስቆም የግድ ነው። ይህን ድርጊታቸውን ካላቆሙ በኢትዮጵያ ሕልውና ላይ እንደቆሙ ይቆጠራል። ስለዚህም በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ የማይደራደረው የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን አረሞች ነቅሎ ሊጥላቸው ይገባል።

መተማመን ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል። እነዚህ አረሞች ተነቅለው መጣል እንዳለባቸው ሁሉም ኢትዮጵያ ሕዝብ ሊተማመንና ወደ እርምጃ ሊገባ ይገባል። መንግሥት ሁሉንም ነገር እንዲያደርግ መጠበቅ የሚያዋጣ አይደለም። መንግሥት የሚያደርገውን መደገፍና አብሮ የጋራ ጠላቶችን ማጥፋት ለማንም የሚተው ተግባር አይደለም።

በሕገወጥነት እና በወንጀል በመጨማለቅ ዘላቂ ትርፍ ማግኘት አይቻልም። ቤተሰብ እንደቤተሰብ እንዲቆም፤ በእኩል መብት መንቀሳቀስ እንጂ አንዱ ሌላውን መደፍጠጥ አይችልም። እኔ ያልኩት ብቻ ትክክል ነው ብሎ ካልተቀበላችሁኝ አድራሻችሁን ላጥፋ የሚለው አባባል ቤት ያፈርሳል እንጂ ቤት አያፀናም።

ኢትዮጵያዊነት የአሸናፊነት እና የነፃነት ምልክት ነው። አሸናፊው የሆነ ቡድን ወይም ብሔር አይደለም። አሸናፊው መላው ሕዝብ ነው። ለሆዱ ያደረም ሆነ እብሪተኛ ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ቦታ የላቸውም። አሁን ላይ የሚያሸንፈው ኢትዮጵያዊነት ብቻ በመሆኑ ከጠላት ጋር ተደራድረው አገር ለማፍረስ የሚሠሩም ሆኑ እኔ ብቻ ልንገሥ የሚሉ ግብዞች ከድርጊታቸው ይታቀቡ። ሕዝብን ዕረፍት የሚነሱ የጥፋት ተግባራት ሊቆሙ ይገባል። ካልሆነ በሀገሩ የማይደራደረው የኢትዮጵያ ሕዝብ እስትንፋሳቸውን መበጠሱ የማይቀር ነው።

# ነፃ ሃሳብ

# በእውቀት እና በኃላፊነት ላይ የተመሰረተ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ለመገንባት

**ታሪኩ ዘለቀ**

በሀገራችን በማህበራዊ ሚድያ የሚሰራጩ የጥላቻና ሀሰተኛ ንግግሮችን በህግ ለመከላከልና ለመቆጣጠር አዋጅ ቁጥር 1185/12 የተደነገገ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ አዋጅ ላይ የጥላቻ ንግግር ማለት በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ቡድን ማንነት ላይ ያነጣጠር ብሄርን፣ ብሄረሰብንና ህዝብን፣ ሃይማኖትን፣ዘርን፣ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ ሆን ተብሎ መድሎን፣ ጥላቻን ወይም ጥቃትን የሚያነሳሳ ንግግር እንደሆነ ያስረዳል፡፡

በተጨማሪም ሀሰተኛ መረጃ መረጃ ማለት፤ ሀሰተኛ የሆነና የመረጃውን ሀሰተኝነት በሚያውቅ ወይም መረጃውን ባሰራጨው ሰው ካለበት አጠቃላይ ሁኔታ አንፃር የመረጃውን እውነትነት ለማጣራት በቂ ጥረት ሳያደርግ የሚሰራጭ ሁከት ወይም ግጭት የማስነሳት ወይም ጥቃት እንዲደርስ የማድረግ እድሉ ከፍ ያለ ንግግር እንደሆነም ያመላክታል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፤በሀገራችን መገናኛ ብዙኃን በተለይም ማህበራዊ ሚዲያዎች በተለያየ መንገድ ጥላቻ አዘል መረጃዎች በአደባባይ ሲሰራጩ ይስተዋላል፡፡ ችግሩ ስራዬ ተብሎ ወይም ባለማወቅ /ከሙያ እጥረት የተነሳ ሊከሰት የሚችልበት ክፍተት ሰፊ ቢሆንም፤ በኛ ሀገር ያለው እውነታ ግን ከችግሩ ፖለቲካዊ ትርፍ ከመፈለግ የመነጨ ስለመሆኑ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም፡፡

በአሁኑ ወቅት የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃዎች ስርጭት ለሀገሪቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት እና ለሰብአዊ ክብር ጠንቅ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይኸው ድርጊት በህዝቦች ዘንድ ያሉ መልካም እሴቶችን በመሸርሸር ለሀገር አንድነት ስጋት እየፈጠረ መሆኑንም በተለያዩ መድረኮች ሲገለፅ ቆይቷል፡፡

ሰሞኑን የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት ያለበትን ሁኔታ የተመለከተ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ይፋ ባደረገበት ወቅት የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ እየተስፋፋ መሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት መቻሉን ግልፅ አድርጓል።

በተለይም ብሄርን ሃይማኖትን እና ፖለቲካዊ አመለካከትን መሰረት በማድረግ ህዝብን በጠላትነት የሚፈርጁ እና አንዱ ለሌላው ስጋት እንደሆነ የሚያስመስሉ የሃሰት መረጃዎች በስፋት መሰራጨታቸውንና የጥላቻ ንግግር አስጊነት ካለፈው አመት አንጻር በይዘትም በአቀራረብም ተባብሶ የቀጠለ መሆኑን በሪፖርቱ አመልክቷል፡፡

እውነታው የሚያሳየው፤ በማህበረሰባችን ዘንድ መረጃዎችን የማጣራት፣የመመርመር፣የማገናዘብ፣ከሌሎች ምንጮች ጋር የማመሳከር ልምድ እጅግ አናሳ መሆኑ ነው፤ ከዚህ የተነሳም የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃዎች በማህበራዊ ሚዲያ ተፅእኗቸው እየበረታ በሀገር ላይ ከፍተኛ ችግር እያስከተለ መሆኑን ነው፡፡

አሁን ላይ አንድ ተፅእኖ ፈጣሪ ወይም አንቂ ሰው የሆነ ይዘትን በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በሚለቀቅበት ሰአት ፅሁፉ እንኳን ተነቦ በማያልቅበት ፍጥነት፣ የተፃፈው ምን እንደሆነ፣ ስለምን እንደተጻፈ ትክክለኛነቱን ሳያጣሩ፣ ሙሉ መልእክቱም ሳይገባን ለሚሊዮኖች ማጋራት ፤በአድናቆት የተሞላ አስተያየት መስጠትም የተለመደ ሆኗል፡፡ከማህበራዊ ሚዲያ ባለፈም አንዳንድ ጊዜ የጋራ በሆነ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ መደበኛ በሚባሉት የመገናኛ ብዙኃን ፅንፍና ፅንፍ የረገጡ ሃሳቦች ሲንፀባረቁ ይታያል፡፡

ከይዘቱ ይልቅ መረጃ ያቀበለውን ሰው ወይም ተቋም በመመልከት ብቻ የጥላቻ ንግግሮችን፣የሀሰት መረጃዎችን ማሰራጨት ተለምዷል፡፡ ችግሩ እንደ ሀገር ይዞ ከመጣው አደጋ አንጻር ማህበረሰቡ መረጃን የመተንተንና የማጣራት ብሎም መርጦ የመውሰድ አቅም እንዲጎለብት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

> **በሀገሪቱ የሚዲያ ነጻነት መኖሩ የተለያዩ መረጃዎች እና ሃሳቦች በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን አማራጮች እንዲሰራጩ የተሻለ እድል ፈጥሯል። ይህ ማለት ግን በስመ ነጻነት የትኛውንም መረጃ እንደፈለግነው የማሰራጨት መብት አለን ማለት አይደለም ። ሌላም አካል ቢሆን የተሳሳቱ መረጃዎችን በየትኛውም ምክንያት ተቀብሎ በስሜትና ባልተገባ መልኩ ማሰራጨት ይችላል ማለት አይደለም**

ሀሰተኛ መረጃን ጨምሮ ሌሎች የጥላቻ ንግግሮች እንደ ሀገር ሊያስከትሉት የሚችለውን ጥፋት ምን እንደሚመስል ማስተማር፣በችግሩ ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው ማስቻል ያስፈልጋል። ችግሩ ሊያስከትል ከሚችለው ጥፋት አንጻር፤ የሚመለከታቸው አካላት ብቻ ሳይሆኑ ዜጎች በሙሉ በኃላፊነት ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

ህዝቡ በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚተላለፉ መረጃዎችን በምን አይነት መልኩ ማጣራት እንዳለበት ፤ የትኛው ሚዲያ አስተማማኝ መረጃ ይሰጣል፣የትኛው ሚዲያ ለማህበረሰብ ጠቃሚ ነው፣የትኛው ሚዲያ ለሀገር ጠቃሚ ነው፣የትኛው ሚዲያ ለሀገርና ለህዝብ የሚሆነውን በጎ ነገርን ያስባል፣ የትኛው ሚዲያ ከግጭትና ከጦርነት ይልቅ በመተሳሰብ በመነጋገር ሰክኖ በማሰብ ትውልድን የመቅረፅ ሚና ይጫወታል፤ በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ የጠራ እውቀት እንዲኖረው ማስቻል ያስፈልጋል፡፡

ትናንት ይሁን ዛሬ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ሀገር እና ህዝብን ለከፍተኛ አደጋ አጋልጦ ብዙ ያልተገባ ዋጋ እንድንከፍል አድርጎናል፡፡ ይህ አደጋ ዳግም እንዳይፈጠር የማስተማር፣ የመመከት፣ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማድረግ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን የተቋቋመው ይህንኑ እውነታ ታሳቢ አድርጎ ነው፡፡

በእርግጥ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ደረጃውን የጠበቀ በሌላው ዓለም ጋዜጠኞች የሚጠቀሙበት የስነ ምግባር ደንብ አውጥቷል፡፡ ይህ ደንብ ለመደበኛው የመገናኛ ብዙኃን ብቻ ሳይሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ዲጂታል ሚዲያ ላይ ለተሰማሩ ጋዜጠኞች ወይም ራሳቸውን እንደ ጋዜጠኛ ለሚቆጥሩ ግለሰቦች መሰረታዊ የሚባል የጋዜጠኝነት ስነ ምግባር ደንብ ነው፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የህግ ጥሰቶችና የስነ ምግባር ግድፈቶች በሚኖሩበት ጊዜ ሊታረሙ የሚችሉበትን ስርአትም አዘጋጅቷል፡፡ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ግለሰቦችን የያዘ የግልግል ዳኝነት አቋቁሟል። በዚህም የጥላቻ ንግግር ጉዳት ደርሶብኛል ወይም አላግባብ ስሜ ተነስቷል፣ ስሜ ጠፍቷል የሚል ማንኛውም ግለሰብ፣ ተቋም ወደ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሄዶ በማመልከት መፍትሄ የሚያገኝበት መንገድ ተዘርግቷል፡፡

ይህም ሆኖ ግን አሁንም ችግሩን ለዘለቄታው መፍታት የሚቻለው፤ህዝቡ በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ መረጃዎችን እውነት ይሁኑ የተሳሳቱ ፤በአግባቡ ተረድቶ የሚያስተናግድበትን ንቃተ ህሊና ማሳደግ ነው። መረጃዎች ከማንም ይምጡ ከማን፣ በጥላቻ የተለወሱ ስላለመሆናቸው ፣ ህብረተሰብን የማይከፋፍሉ እና በቂ መረጃ የሚቀርብላቸው ተአማኝ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ የሚችልበትን ባህል መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

አሁን ላይ እንደሀገር እያጋጠሙን ያሉ ችግሮች በአንድም ይሁን በሌላ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት ጋር የተያያዙ ከመሆናቸው አኳያ፤ ችግሮቹን ለመሻገር የመገናኛ ብዙኃኑ ኃላፊዎች በተለይም በርካታ ተከታይ ያሏቸው የማህበራዊ ሚዲያ ባለቤቶች በኃላፊነት መንገድ ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡

በሀገሪቱ የሚዲያ ነጻነት መኖሩ የተለያዩ መረጃዎች እና ሃሳቦች በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን አማራጮች እንዲሰራጩ የተሻለ እድል ፈጥሯል። ይህ ማለት ግን በስመ ነጻነት የትኛውንም መረጃ እንደፈለግነው የማሰራጨት መብት አለን ማለት አይደለም ። ሌላም አካል ቢሆን የተሳሳቱ መረጃዎችን በየትኛውም ምክንያት ተቀብሎ በስሜትና ባልተገባ መልኩ ማሰራጨት ይችላል ማለት አይደለም፡፡

ይህ አይነቱ አካሄድ ለተጀመረው የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ዋነኛ ፈተና እየሆነ ነው፡፡የጀመርነው የዲሞክራሲ ስርአት ከሁሉም በላይ በመገናኛ ብዙኃን አካባቢ ያሉ አካላትን እና ባለሙያዎችን በኃላፊነት መንቀሳቀስ የሚጠይቅ ነው። መላው ህዝባችንም ቢሆን ፤ ሀሰቱን ከእውነት፣ስሜቱን ከስክነት ተደበላልቀው የሚሰራጩ መረጃዎችን በአግባቡ የመለየት ኃላፊነት አለበት፡፡

በእርግጥ የማህበራዊ ሚዲያዎች መስፋፋት ዓለምን ወደ አንድ መንደርነት እያቀራረባት ይገኛል፡፡ በዚህም የሰው ልጆች የሚዲያና የፖለቲካ ተሳትፎም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ባህልን ለማሳደግና ህይወትን ለማቅለል የተሻሻለ እድል ይዞ እንደመጣ ችግር ይዞ መምጣቱ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ በችግሩ በእድገት ወደ ኋላ በቀሩት ሀገራት አመዝኖ ይስተዋላል፡፡

በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ብዝሃነት ባለባቸው ሀገራት ፤ሀገረ መንግስቱን ለማስቀጠል ሆነ ህዝቦች የሚፈልጉትን ልማት እውን ለማድረግ ማህበራዊ ሚዲያውን በኃላፊነት መንፈስ መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡ ከሰላምና አብሮነት ይልቅ ጦርነትንና መለያየትን፣ግጭትና ጥላቻን በማህበራዊ ሚዲያዎች ማቀንቀን ከቁጥጥር ውጪ ሊሆን የሚችል አደጋ ይዞ መምጣቱ የማይቀር ነው ፡፡

ከቅርብ አመታት ወዲህ ከጥላቻና ያልተገቡ መልእክቶች ባለፈ አሰቃቂና ፀብ አጫሪ ምስሎችን በፌስቡክና መሰል ማህበራዊ ሚዲያዎች መመልከት የየእለት አጋጣሚያችን ሆኗል፡፡ እነዚህ በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚሰራጩ የውሸት መልእክቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ካለው መረጃን የማጣራት ባህል አናሳነት የተነሳ እንደ እውነት የመወሰዳቸው አጋጣሚ ሰፊ ነው። በዚህም የሀገሪቱ ሰላምና የህዝቦቿ በጋራ የመኖር እሴቶች እየጸጎዱ ነው፡፡ ችግሩ የህዝቦችን አብሮነትን ከመሸርሸር አልፎ ለህይወት መጥፋትና ንብረት መውደም ምክንያትም እየሆነ ነው፡፡

በተለይም አብዛኛው በሚባል ደረጃ ወጣቱ ትውልድ የማህበራዊ ሚዲያን ጥቅም የተረዳበት መንገድ ትክክለኛ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ብዙዎቹ እየተጠቀሙት ያሉት ለመሰዳደብ፣ ለመኮራረጅ፣ አንዱ ማኅበራዊ ሚዲያን ተጠቅሞ ብዙ ሰው ሲያንቀሳቅስ ሲያዩ እነሱም እንደዛ ለመሆን ለመሞከር ነው። በአብዛኛው የማኅበራዊ ሚዲያን ዋጋ እና ጥቅም በማወቅ እና በማስተዋል ሳይሆን የጊዜያዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት እና ለማርካት ሲጠቀሙበት ይስተዋላል።

በመሆኑም አጠቃቀሙ ስርአት ያስፈልገዋል፡፡ ስርአት የምንለው ነገር ለዘለቄታዊ ጥቅም ጊዜአዊ ፍላጎትን መግታት ነው። ስለዚህ ወጣቶች የትምህርት መጽሐፍቶችን ማንበብ ለዘለቄታ የሚሆን ነገርን መሥራት ሲገባቸው ከጠዋት እስከ ማታ አንዳንድ ጊዜ እንደውም እስከ ሌሊቱ ዘጠኝና አስር ሰአት በዋይፋይ እየተጠቀሙ ቀን ላይ ደግሞ ስድስት ሰአት፣ ሰባት ሰአት የሚነሱና ምግብ የሚጠይቁ ልጆች እንዳሉ እየተመለከትን ነው።

ማህበራዊ ሚዲያው በእውቀት፣ በህግ / በተጠያቂነት በጠንካራ ዲሲፒሊን ካልተመራ ፤ሊያስከትለው የሚችለው ጥፋት ሀገርን ህዝብን ያልተገባ ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ የሀገር ህልውና ስጋት ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ለዚህ ደግሞ በዚህ ችግር ምክንያት ትናንት የከፈልነውን፤ ዛሬም እየተፈታተነን ያለውን አደጋ በስክነት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

የማህበራዊ ሚዲያው በህግና በተጠያቂነት እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በእርግጥ ኢትዮጵያ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ህግ እያረቀቀች መሆኑ ከተሰማ አመታት ቢቆጠርም መሬት ላይ ወርዶ ማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ፈር የሚያሲዝ ነገር አልተገኘም፡፡ ስለዚህ በሌሎች ሀገራት እንደምናየውን የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ህግ እንዲኖር ማድረግ ለነገ የሚባል ተግባር መሆን የለበትም፡፡

አሁን ላይ ዘመኑ የሰጠውን ቴክኖሎጂ በልኩና በተገቢው መንገድ በማስተናገድ በእውቀት እና በኃላፊነት ላይ የተመሰረተ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ለመገንባት፣ ከሁሉም በላይ የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎችን ንቃተ ህሊና ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ማህበረሰቡም መረጃን እንዳለ በመውሰድ እራሱን ከዛም ባለፈ ሀገሩን አደጋ ውስጥ ከሚከት አካሄድ መቆጠብ አለበት፤ ለዚህ ደግሞ ቆም ብሎ ማሰብ ይኖርበታል፡፡

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ታዳሽ ኃይል- አዳዲሶቹ የፈጠራ ባለሙያዎቹ ግኝቶች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ወጣት ሆሄያት ብርሃኑ እና ዮሐንስ ዋሲሁን ከቡና ገለባ እና ከሰጋቱራ ከሰል የሚያመርት ማሽን እንዲሁም ‹‹ቅልብጭ›› የተሰኘ የከሰል ምድጃ የፈጠራ ባለቤቶች ናቸው። እነዚህን የፈጠራ ሥራቸውን ለማሳደግ በማሰብ በ2015 ዓ.ም ‹‹ሽስኪ ኢነርጂ እና ቴክኖሎጂ ፒኤልሲ›› የተሰኘ ድርጅት መስርተዋል። ድርጅቱም የታዳሽ ኃይልና ንፁህ የማብሰያ መፍትሔዎች ለማቅረብ የተመሰረተ ነው።

ባለሙያዎቹ በታዳሽ ኃይል የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እየሰሩ ሲሆን፤ ከቡና ገለባ እና ከሰጋቱራ ከሰልን የሚተኩ ማገዶዎች ቀዳሚዎቹ ናቸው። በተጨማሪም ‹‹ቅልብጭ›› የሚል ስያሜ የሰጡትን የከሰል ምድጃ እያመረቱ በማከፋፈል ላይ ይገኛል።

እነ ሆሄያት የፈጠራ ስራውን ከጀመሩ ሦስት ዓመታት ያህል አስቆጥረዋል። የፈጠራ ሀሳቡን ለማመንጨት መነሻ የሆናቸውን አጋጣሚ የተፈጠረላቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመካኒካል ኢንጂነሪንግ ምህንድስና ትምህርት ተማሪ በነበሩት ወቅት ነው።

በወቅቱ ለሥራ ላይ ልምምድ (internship) የቡና አምራች አርሶ አደሮች አካባቢ የመሄድ አጋጣሚ ይፈጠርላቸዋል። በገዝወ ለቡና አምራች አርሶ አደሮች ስልጠና የመስጠት እድልም ያገኛሉ። ስልጠናውን በሚሰጡበት ወቅት ‘አርሶ አደሮች ቡና ሲያመርቱ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች አንዱ የሆነው የቡና ገለባ ክምችት መብዛት’ እንደሆነ አርሶ አደሮቹ ሲናገሩ ይሰማሉ። የአርሶ አደሮቹን ችግር ካዳመጡ ጊዜ ጀምሮ እነ ሆሂያት አላረፉም፤ ለችግሩ መፍትሔ ለመፈለግ በጥልቀት በማሰብ የመፍትሔ ሀሳብ ማመንጨት ውስጥ ይገባሉ።

ወጣቱ የፈጠራ ባለሙያ ሆሄያት እንደሚለው፤ ኢትዮጵያ በቡና ምርት በዓለም አምስተኛ ስትሆን በአፍሪካ ደግሞ አንደኛ ናት። በመሆኑም በዓመት በጣም ብዙ የቡና ምርት ይመረታል። ከሚፈለፈለው ቡና የሚወጣው ገለባ ደግሞ በርካታ ነው። ይህም በቡና አምራች አርሶ አደሩ አካባቢ ላይ ብዙ ችግሮች እያደረሰ ይገኛል። ‹‹የቡና ገለባው አካባቢውን በመሙላት ቦታ ይይዛል፤ ሲቆይ ደግሞ የሚሸት ሲሆን የአካባቢ ላይ ለሚኖረው ማህበረሰብ ለተለያዩ አይነት ህመም ይዳርጋል። እንዲሁም ብዙ ተያያዥ ችግሮች ሊያስከትል እንደሚችል አርሶ አደሮቹ በሰጡን መረጃ መረዳት ችለናል›› ይላል።

እነ ሆሄያት ለአርሶ አደሩ ችግር መፍትሔ ለመፈለገ ባደረጉት ጥረት የቡና ገለባን ወደ ኢነርጂ መቀየር የሚችል ማሽን ዲዛይን በማድረግ ለመስራት ችለዋል። አዲሱ ማሽን ከቡና ገለባ ፔሌት የሚባሉ እንደ ከሰል አይነት የማገዶ እንክብሎችን ማምረት የሚችል ነው። ማሽኑን በሀገር ውስጥ ያሉ ጥራት ያላቸው ቁሳቁስን ተጠቅመው የሰሩ ሲሆን፤ በየጊዜውም ማሻሻያ እየተደረገለት እያደገና አሁን ያለውን ቅርጽና ይዘት ሊኖረው ችሏል።

ማሽኑን የመስራቱ ሀሳብ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተጸነሰ ሀሳብ እንደመሆኑ እቅዱን በማዳበር ዲዛይን በማውጣት ወደ ሥራ ለማስገባት ሦስት ዓመታት መፈጀቱን ሆሄያት ያመላክታል። ይህ ከቡና ገለባና ሰጋቱራ የማገዶ እንክብሎችን ማምረት የሚችለው ማሽን በመጀመሪያ በትንሹ ለሙከራ ያህል የተሰራ ሲሆን፤ ይህንን አሻሽሎ በትልቁ በመስራት ከሰጋቱራ የማገዶ እንክብሎችን እንደሚያመርት ያስረዳል።

አሁን ማሽኑ ከቡና ገለባ ማገዶ እያመረተ ባይሆንም፣ ከሰጋቱራ ማገዶን በማምረት ወደ ጥቃቅን ማገዶ (ወደ ፔሌቶች) እየቀየረ ይገኛል። ማሽኑ ከቡና ገለባ ማምረት አቅቶት ሳይሆን አሁን ባለበት አካባቢ ሰፊ ክምችት ያለው ሰጋቱራ በመሆኑ ነው ብሏል። በቀጣይ ደግሞ ከቡና ገለባ ፔሌቶች ያመርታል ሲል ሆሄያት አስታውቋል።

ሌላው የፈጠራ ውጤታቸው ደግሞ ‹‹ቅልብጭ›› የሚል ስያሜ የተሰጠው የከሰል ምድጃ ነው። ምድጃው የተሰራው ሀገር ውስጥ ከሚገኙ ቁሳቁስ



‹‹ቅልብጭ››የሚል ስያሜን የተሰጠው የከሰል ምድጃ

ሲሆን፣ ብረት፣ ፋይበር ግላስ እና ጋልባናይዝድ ስቴል በመጠቀም ተሰርቷል፡ ‹‹ቅልብጭ ምድጃ›› ከሰል ቆጣቢ ነው፤ ዙሪያው የተሞላው ኦቪን፣ ዳቦ መጋገሪያ እና ማቀዝቀዣ ፍሪጅ ውስጥ የሚገኝ ፋይበር ግላስ በተሰኘ ቁስ ነው። ‹‹ንጹህ የማብሰያ መፍትሔዎች ማቅረብ ሲባል ማገዶውን ማቅረብ ብቻ ሳይሆን፣ ምድጃም በጣም ወሳኝ ነው፤ እኛም ሁለቱንም ማቅረብ ችለናል›› ይላል ሆሄያት።

የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ እንደሚያመላክተው፤ የቤት ውስጥ የአየር መበከል ዓለም ችግር እየሆነ መጥቷል፤ የቤት ውስጥ የአየር ብክለት በዓለም በዓመት እስከ አራት ሚሊዮን ሰዎች እየገደለ ነው። በኢትዮጵያም እንዲሁ የቤት ውስጥ የአየር መበከል(indoor pollution) ችግር እየሆነ ከመምጣቱ በላይ በዓመት ከ50ሺ በላይ ሰዎች በዋናነት ደግሞ ሴቶችን ይገድላል። የአገሪቱን የሞት ምጣኔ አምስት በመቶውን የሚይዘውም ይሄው የቤት ውስጥ የአየር መበከል ሆኗል።

ጉዳቱ የሚከሰተው በቤት ውስጥ ለማገዶነት በምንጠቀመው የከሰል እና የእንጨት ጭስ ምክንያት ነው። ለዚህ ችግር መፍትሔ ለማበጀት የተሻሻለ ምዳጃ ላይ መስራት ወሳኝ መሆኑን በማመን እነ ሆሂያት ይህን የፈጠራ ቴክኖሎጂ ሰርተዋል።

ሆሄያት እንደሚለው፤ ምድጃው ከተለያዩ ጥራት ካላቸው ቁሳቁስ ነው የሚመረተው። ምድጃው በጥራት የሚመረት ሲሆን፤ ጥራትን ከዋጋ ጋር አዋህዶ በተመጣጣኝ ዋጋ ህብረተሰቡ ሊጠቀምበት እንዲችል ተደርጎ ተሰርቷል። ሌሎች ከውጭ የሚገቡ የተሻሻሉ ምድጃዎች እንዳሉ ጠቅሶ፤ ይህ ምድጃ ግን ከእነዚህ በጣም በተሻለ ጥራት እና በቅናሽ ዋጋ ተመርቶ ለህብረተሰቡ የቀረበ ነው ብሏል።

ምድጃዎቹም ትንሹ አንድ ሺ 300 ብር፣ መካከለኛው አንድ ሺ700 ብር እና በመጠን ከፍ ያለው ደግሞ ሁለት ሺ300 ብር የዋጋ ተመን ወጥቶላቸው ለገበያ እየቀረቡ መሆናቸውን ወጣት ሆሄያት አስታውቋል። ምድጃውን ህብረተሰቡ ዘንድ ተደራሽ በማድረግ ለገበያ ማቅረብ ከተጀመረ ሰባት ወራት ያህል እንደተቆጠሩ ጠቅሶ፤ ምድጃው ከሰልን በጣም እንደሚቆጥብ ተናግሯል። ይህ ጠቀሜታው በፍጥነት ተቀባይነትና ተወዳጅነት እንዲያገኙ እንዳስቻላቸው አስታውቆ፣ ተደራሽ በሆነባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ የገበያ ፍላጎት እንዳለም ይገልፃል ።

እንደ ሆሄያት ማብራሪያ፤ አሁን ላይ ምድጃው በአዲስ አበባ እና በዙሪያ ባሉ ከተሞች እንዲሁም በሀዋሳ ከተማ እና በተለያዩ ከተሞች ተደራሽ እየተደረገ ነው። ምድጃው ጥራት ካለው ቁሳቁስ ስለሚሰራ ማገዶ ቆጣቢ ነው። በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ከ700 በላይ ምድጃዎች ለገበያ ቀርበው ተሸጠዋል።

‹‹ምድጃውን እየተጠቀሙ ያሉ ደንበኞችም ምድጃው ከሰል እንደቆጠበላቸው እና ሲታይም ውበት እንዳለው ይነግሩናል›› የሚለው ሆሄያት፤ ይህን ታዳሽ ኃይል በተለይ ለገጠሪቱ የአገሪቱ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ እየሰሩ መሆናቸውን ገልጿል። ባለፉት ሳምንታት መንግሥታዊ ካልሆነ አንድ ድርጅት ጋር በመተባበር በዳውሮ፣ በበደሌ እና በመሳሳሉት የገጠሪቱ የአገሪቱ አካባቢዎች ለሚገኙ ማህበረሰቦች ምድጃውን የማስተዋወቅ ሥራ መስራቱን አስታውቋል።

የምድጃውን አጠቃቀም ጭምሮ በማሳየት ህብረተሰቡ የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት እያደረጉ መሆናቸውንን አብራርቶ፣ ህብረተሰቡ ቁጠባ ማድረግ እንዲችልና ብድር ተመቻችቶለት ምድጃዎቹን መግዛት የሚችልበት ሁኔታ እየመቻቸ እንደሆነም አስታወቋል።

ከእነዚህ በተጨማሪ ሌሎች የፈጠራ ሥራዎችንም መስራታቸውን የሚገልጸው ሆሂያት፤ በገጠሪቷ የአገሪቱ አካባቢዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ ‹‹ሮኬት ስቶቭ›› የተሰኘ በእንጨት የሚሰራ ምድጃ አንዱ መሆኑን ይናገራሉ። ይህ የፈጠራ ሥራ የማገዶ ፍጆታ በጣም ይቀንሳል፤ ጭስ የሚቀንስና ጥራት ያለው ምርት መሆኑንም ተናግሯል።

እነ ሆሄያት ‹‹ኢንስቲትዩሽናል ስቶቭ›› የተሰኘ ሌላ ምድጃንም እያመረቱ ይገኛሉ። ይህ ምድጃ በተለይ ለዩኒቨርሲቲዎች፣ ለትምህርት ቤቶች ፣ለስደተኛ ኮምፓች እና ለብዙ ሰዎች ምግብ ለሚያዘጋጁ መሰል ተቋማት የሚያገለግል መሆኑን ጠቅሶ፣ ይህ ምድጃ በሰፊው ምግብ ለማብሰል የሚያስችል ከመሆኑም በላይ ማገዶ ቆጣቢ መሆኑን ተናግሯል።

እነ ሆሄያት፤ የታዳሽ ሃይልና የማብሰያ ቴክኖሎጂ ላይ ብዙ ሥራዎች ለመስራት አቅደዋል። በዚህ ረገድም እስካሁን ሠርተው ለገበያ ያቀረቧቸውን የፈጠራ ውጤቶች /Technology/ በየጊዜው ለማሻሻልና ለማዘመን እንደሚሰሩ ጠቅሶ፣ በአሁኑ ወቅት የህብረተሰቡን ኑሮ ሊያሻሽሉና ሊያቀሉ የሚችሉ የምርምርና የፈጠራ ሥራዎች መስራቱን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመልክተዋል። እነዚህ ቴክኖሎጂዎችንም በብዛት በማምረት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ይገልጻል።

‹‹አሁንም በሙከራ እና ዲዛይን ደረጃ ላይ ያሉ የተለያዩ የፈጠራ ውጤቶችን እየሰራን ነው›› የሚለው ሆሄያት፤ እነዚህን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ቀስ በቀስ እያሳደጉ የሚፈለገው ውጤት ላይ ሲደርሱ ለህብረተሰቡ ይፋ እንደሚደረጉ አስታውቋል። በቀጣይ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ያሉ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል የፈጠራ ሥራዎች እቅድ እንዳላቸው አመላክቷል።

ከመነሻ ንግድ ስራ የፈጠረ ሀሳብ /Startup/ ተነስተው እየሰሩ ያሉት ሥራ ህብረተሰቡ ዘንድ ደርሶ ውጤት እያመጣ መሆኑን በተጨባጭ እየተመለከቱ መሆናቸውንም ሆሂያት ጠቅሶ፣ ይህ ደግሞ ለስራው የበለጠ መነሳሳት እንደሚፈጥር ተናግሯል። ህብረተሰቡ ምድጃዎቹን ለመጠቀም ያለው ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሶ፣ ምድጃዎቹን በስፋት በማምረት ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል ብሏል።

አሁን እነዚህን ምርቶች በተለያዩ የገበያ ቦታዎች እየተሸጡ መሆናቸውን ገልጾ፤ ምርቶቹን ሰዎች የሚፈልጉበት ቦታ ድረስ በማቅረብ ላይ እንደሚገኙም ይናገራል። ‹‹የህብረተሰቡን ፍላጎት በማርካትና ተደራሽነታቸውን በማስፋት ለሚያደርጉት ጥረት ሀሳባቸውን በመደገፍ አብሮ መስራት የሚፈልግ ድርጅት ካሉ ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጧል።

ሆሄያት እንደሚለው፤ የፈጠራ ስራቸውን እዚህ ደረጃ ለማድረስ ብዙ ወጣ ወረዶችን ማለፍ የግድ ብሏቸው እንደነበር አስታውሶ በተደጋጋሚ በመሞከር እና ብዙ ጥረት በማድረግ የሚፈልጉትን ማሳካት እንደቻሉ ሌሎቸም ይህንን መንገድ ቢከተሉ ውጤታማ እንደሚሆኑ ተናግሯል።

‹‹የፈጠራ ሥራ ሁልጊዜ መሻሻል ማሳየትን ይጠይቃል፤ ሥራዎቻችን በአንዴ ጊዜ እዚህ ደረጃ ላይ አልደረሱም፤ ከአራትና ከአምስት ጊዜያት በላይ ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፤ የማሻሻል ሂደት አይቆምም፤ አሁንም የምናሻሽለው ካለ ይቀጥላል›› የሚለው ሆሄያት፤ የፈጠራ ሥራዎቻቸውን በየጊዜው ለማሻሻል ጥረት እያደረጉ እንደሚገኙ አመልክቷል።

የኢኖቬዝ-ኬ ኢትዮጵያ ማዕከል እና ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በጋራ ባዘጋጁት መነሻ ንግድ ስራ የፈጠረ ሀሳብ /Startup/ ፕሮግራም ላይ ሀሳባቸው አሸናፊ ሆኖ ለመሳተፍ እድሉ ማግኘታቸውን ሆሄያት ጠቅሶ፣ በዚህም በየሁለት ሳምንቱ ባለሙያዎች ያሉበትን ሂደት በመመልከት ድጋፍ እያደረጉላቸው ለአምስት ወራት ያህል የማማከር አገልግሎት እንደተሰጣቸው አስታውቋል። ይህ ብዙ ነገሮች እንዲያስተካክሉ እንደረዳቸው እና ከጀማሪ የስራ ፈጣሪነት ተነስተው አሁን ያሉበት ደረጃ ለመድረስ እንደቻሉ ሆሂያት ተናግሯል።

በፈጠራ ሥራ ላይ መሰማራት የሚፈልጉ ጀማሪ የፈጠራ ባለሙያዎች የመነሻ ንግድ ስራ የፈጠረ ሀሳብ ያላቸው /Startup/ መጀመሪያ ለመፍታት የሚፈልጉት ችግር በደንብ አውቀው መፍትሔ ለማምጣት መስራት አለባቸው ሲል ሆሂያት ይገልጻል፤ በአካባቢያቸው እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ችግሮችን በሚገባ ከመረዳት ባሻገር ለችግሩ የተገኘን መፍትሔ ህብረተሰቡ ተቀብሎ ሊጠቀምበት የሚችለው ነው እንዴ የሚለውን በጥልቀት ማጤን አስቀድሞ መስራት ያለበት የቤት ሥራ መሆኑን ይጠቁማል።

ምርታቸው አንድ ጊዜ እንደተሰራ በዚያው የሚቀጥል ሳይሆን፣ ሁልጊዜ እያሻሻሉ እና ዘመኑ በሚጠይቀው ልክ እያዘመኑ መምጣት ያስፈልጋቸዋልም ብሏል። ሥራቸው ውጤት አፍርቶ ምርቶታቸው ለገበያ ላይ ሲቀርቡ ደግሞ የምርቶቻቸውን ተጠቃሚዎች አስተያየት በመቀበል የተሻለ ሥራ መስራት አለባቸው። ለዚህም ሁሌጊዜም ምርቶቻቸውን እያሻሻሉ መገኘት አለባቸው ሲል ይመክራል።

ጀማሪዎች ያላቸው የቴክኖሎጂ እውቀት ብቻ ሊሆን እንደሚችል ገልጾ፤ ከዚህ ጋር ቢዝነሱን አብሮ ማስኬድ እንደሚጠይቅም አመልክቷል። ከቢዝነስ አማካሪ ተቋማት ጋር መስራት ሥራቸውን ወደ ገበያ ማሳደግ እንደሚያስችላቸው አስገንዝቧል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የአፈር አሲዳማነት መጨመርና የግብርናው ዘርፍ ተግዳሮት

አስመረት ብስራት

የኢትዮጵያ የአፈር ሀብት መረጃ ፕሮጀክት ጥናት መሰረት እየታረሰ ካለው የመሬት ሽፋን 43 በመቶው በአሲዳማነት የተጠቃ ነው። ከዚህ ውስጥም 28 በመቶ ጠንካራ አሲዳማ ሲሆን ይህም አጠቃላይ ከሚታረሰው መሬት ሦስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር ይሸፍናል።

በሀገራችን ዋነኛው የኢኮኖሚ ምንጭ ግብርና መሆኑ ይታወቃል። ይህን ዋና የሀገር ኢኮኖሚ ምሰሶ የሆነውን ግብርና ለማስፋፋት ብሎም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የአፈር ጤናን መጠበቅ የህልውና ጉዳይ ተደርጎ መታየት እንዳለበት የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ታዲያ ይህን የኢኮኖሚ ዋልታ የሆነ የግብርና ዘርፍ በአፈር አሲዳማነት የተነሳ እየተጎዳ ከሆነ ኢኮኖሚው ላይ የሚኖረው ተፅእኖ ምን ሊሆን ይቻላል? ይህን የአፈር ለምነትን መቀነስ እና የሚያስከተለው ችግር በምን መልኩ ይቀረፋል ? እና ሌሎች ጥያቄዎችን ይዘን የዘርፉን ባለሙያዎች አነጋግረናል። ከምላሻቸው ጋር መልካም ቆይታ።

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ሶፊያ ካሳ (ዶ/ር) እንደሚያብራሩት ፤ የአፈር ኬሚካዊ ይዘት (ፒኤች) ከሚጠበቀው በታች ሲሆንና የአልሙኒየም ንጠረ ነገሮች በሚበዙበት ጊዜ የአፈር አሲዳማነት ይከሰታል። የአፈርን ኬሚካዊ ይዘት አማካይ ሊያደርጉ የሚችሉ እንደ ማግኒዢየም፣ ፖታሺየም፣ ካልሺየም ያሉ ንጥረ ነገሮች በተለይ ከፍተኛ ዝናብ በሚዘንብባቸው አካባቢዎች በዝናብ ታጥበው መጠናቸው ስለሚቀንስ ለአሲዳማ አፈር መፈጠር ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዙ ይጠቁማሉ። የእርሻ ድግግሞሽ መብዛትና፤የአፍርና ውኃ ጥበቃ ሥራዎችን በአግባቡ አለመስራትና የተዛባ የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ አጠቃቀም ለአሲዳማ አፈር መፈጠር መንስዔ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ክፍል የተክሎች ባይሎጂ እና ባዮ ዳይቨርስቲ መምህር የሆኑት ዶክተር የወንደሰን ጠና በበኩላቸው የአፈር አሲዳማነት ማለት አሲዳማ አፈር የአፈሩ ኬሚካላዊ ይዘት ወይም ፒ ኤች (pH) መጠን ከሰባት በታች የሆነ እና የሃይድሮጅን ($H^+$) እና አልሙኒየም ($Al^{+3}$) ንጥረ- ነገሮች የሚበዙበት አፈር ማለት ነው።

በአፈር ሳይንስ እና ፕላንት ኒውትሬሽን ላይ በርካታ ጥናቶች ያደረጉት ዶክተር ጠና የአፈር አሲዳማነት በሀገራችን በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ጫና እያሳደረ የሚገኝ የአፈር ለምነት ችግር ሲሆን፤ ከፍተኛ ዝናብ የሚያገኙና በምርታማነታቸው የተሻሉ ናቸው የሚባሉትን የሀገሪቱን አካባቢዎች ጭምር እየጎዳ መሆኑንም ነው የሚጠቁሙት።

የአፈር ጤንነት ችግሮች በሦስት ዋና ዋና መንገዶች ይገለፃሉ። ይኸውም አሲዳማነት፣ የጨዋማነት ችግር የሚነሳበትና ኮትቻማ/ጥቁር ወይም መረሬ አፈር/ ብሎ ማስቀመጥ እንደሚቻል ዶክተር የወንደወሰን ይናገራሉ። በኢትዮጵያ ከ15 ሚሊዮን ሄክታር በላይ የሚታረስ መሬት ሲኖር ወደ 7 ነጥብ 5 ሚሊየን ሄክታር መሬት በአሲዳማነት የተጠቃ እንደሆነ ነው የጠቀሱት።

አፈር ሰብሎች የሚፈልጓቸውን ንጥረ-ነገሮች በተሟላና በተመጣጠነ መልኩ ሳይዝ ሲቀር ምርታማነት ጥያቄ ውስጥ እንደሚወድቅ የሚናገሩት ዶክተሩ፤ ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ከ1 ሚሊየን ሄክታር በላይ መሬት በአፈር አሲዳማነት ክፉኛ የተጎዳ በመሆኑ ምርታማነቱ ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ የሚቀመጥ መሆኑን ይጠቁማሉ። እፅዋት ከአየር፣ ውሃና የፀሐይ ብርሃን በተጨማሪ 18 ዓይነት ንጥረ-ነገሮችን ከአፈር ውስጥ ሊያገኙ እንደሚችሉ የሚናገሩት ዶክተር የወንደወሰን የአፈርን ደህንነት መጠበቀ የግድ የሚል ተግባር መሆኑ ይናገራሉ።

የአፈር አሲዳማነት መንስኤዎች የሚባሉ በዋነኝነት የዝናብ መብዛት፣ የአፈር መሸርሸር፣ የሰብል ተረፈ-ምርት ሙሉ በሙሉ ከማሳ ማንሳት እና ፍግ አለመጠቀም፣ እንዲሁም አሲዳማ ዝናብ የመሳሰሉት አፈር ውስጥ ያሉ ለተክሉ እድገት ጠቃሚ ንጥረ-ነገሮች እንዲሟጠጡ እንደሚያደርግ በመንስኤነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን ይናገራሉ።

እንደ ዶክተር የወንድወሰን ገለፃ የአፈር አሲዳማነት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስተዋል ሲሆን በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ተጠቃሽ ናቸው።



ዶክተር የወንድወሰን ጠና



ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኽ ተስፋ

ይህን ችግር የሚያስከትለውን የአፈር አሲዳማነት ለማከም ኖራ ዋናው መፍትሄ መሆኑን የተናገሩት ዶክተሩ አሲዳማ አፈርን ለመከላከል በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ መንገዶች ከሚወሰዱ እርምጃዎች ባሻገር አፈሩን በኖራ የማከም ሥራ በዋናነት ተመራጭ ነው ይላሉ።

የተለያዩ አፈርን የማከሚያ ግብአቶች ያሉ ቢሆንም በቀላሉ ከመገኘትና ከዋጋው ርካሽነት አንፃር ካልሽየም ካርቦኔት ወይም "የግብርና ኖራ" እየተባለ የሚጠራው በስፋት አገልግሎት ላይ እንደሚውል ገልጸዋል።

ወደ 15 ነጥብ 6 ሚሊየን ሄክታር የሚታረስ መሬት ሲኖር፤ ከዚህ ውስጥ 7 ነጥብ 5 ሚሊየን ሄክታር ወይም ከ43 በመቶ የማያንሰው በአሲዳማ አፈር የተጠቃ መሆኑን ጠቅሰው፤ ወደ 4 ሚሊየን ሄክታር የሚሆነው በጠንካራ አሲዳማነት የተጠቃ እንደሆነና በኖራ መታከም ያለበት መሆኑን አስረድተዋል።

ጠንካራ አሲዳማ አፈር ስንል የአፈሩ ኬሚካላዊ ይዘት ወይም ፒ ኤች (pH) መጠን ከ 5 ነጥብ 5 በታች የሆነ እና የሃይድሮጅን ($H^+$) እና አልሙኒየም ($Al^{3+}$) ካታዮኖች የሚበዙበት አፈር ሲሆን፤ የእነዚህ ካታዮኖች መብዛት የሰብሎችን ሥር በመመረዝ በዕድገታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን እንደሚፈጥር ባለሙያው ይናገራሉ።

ፒ ኤች መጠኑ ከሰባት ወደ ዜሮ እየቀነሰ ሲሄድ የአሲድነቱ ጥንካሬ የሚጨምር ሲሆን ከሰባት ወደ 14 ሲጨምር የጨዋማነቱ ባህሪ እንደሚጨምር ነው የሚያስረዱት። በአገራችን ሁኔታ አሲዳማ አፈርን ለማከም ኖራ መጠቀም የሚያስፈልገው የአፈሩ ፒ ኤች መጠን ከ5 ነጥብ 5 በታች ሲሆን ነዉ። ኖራ በተፈጥሮ የሚገኝ የካልሲየም እና የማግኒዚየም ካርቦኔት ሃይድሮኦክሳይድ ውህድ ሲሆን፤ አሲዳማ አፈር ውስጥ በሚጨመርበት ወቅት አሲዳማ አፈር ውስጥ የሚገኙትን አልሙኒየም እና ሃይድሮጂን አሉታዊ እንቅስቃሴዎችን በመግታት የአፈሩን ፒ ኤች መጠን ከፍ በማድረግ ለእፅዋት እድገት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በአማካይ በአፈር አሲዳማነት የተጎዳ መሬትን ለማከም በሄክታር 30 ኩንታል የግብርና ኖራ እንደሚያስፈልግ የሚናገሩት ዶክተር የወንድወሰን በአሲዳማነት የተጠቃ መሬት አሲዳማነትን የሚቋቋሙ ሰብሎች ካልተዘሩበት ወይም አፈሩን በኖራ የማከም ሥራ ካልተሰራ የሚሰጠውን የአፈር ማዳበሪያ ከጥቅም ውጭ በማድረግ ለኪሳራ ይዳርገናል ነው ያሉት።

ከዚህም በተጨማሪ የሰብልን ተረፈ ምርቶች ማሳው ላይ በመተው፤ የተፈጥሮ መዳበሪያዎችን በመጠቀም ቀይጥ ማዳበሪያዎችን መጠቀም የአፈርን አሲዳማነት ለመቀነስ መፍትሄ መሆኑን አስቀምጠዋል። ከዚህም በተጨማሪ አሲዳማ አፈር የሚስማማቸውን ሰብሎች አሲዳማ አፈር ያለበት አካባቢ መትከል ተጠቃሚ ያደርጋል ብለዋል።

ይህም ሲባል ቡና አሲድ ያለባቸው አካባቢዎች ቢዘራ ምርታማነቱን አይጎዳውም። ከዚህም በተጨማሪ ሻይ ቅጠልም በአሲዳማ አፈር ላይ ጥሩ ምርት የሚሰጥ ሲሆን፤ ድንችም እንደዚሁ የአሲድ መሬት ላይ ቢተከል የተሻለ ምርት ይሰጣል ብለዋል።

**የተሻለ ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ምርት ከለም መሬታችን ይታፈስ ዘንድ የአፈር አስዳማነትን የሚጨምሩ ተግባራትን ከመፈፀም መቆጠብ ይገባል**

የምጣኔ ሀብት ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸ ተስፋ በጉዳዩ ላይ በሰጡት ሀሳብ የአሲዳማነት መጨመር ምክንያቶች ወይም የአፈርን አሲድነት የሚጨምሩ አራቱ ዋና ዋና ምክንያቶች እንዳሉ ይዘረዝራሉ። እነዚህም ከእርሻ ማስወገድ፤ ናይትሮጅንን እና ናይትሬት ከዕፅዋት በታች ማፍሰስ፤ የናይትሮጅን ማዳበሪያዎች ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም፤ የኦርጋኒክ ቁስ መገንባት ናቸው ብለዋል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንደሚሉት የአሲድነት አካላዊ መገኘት የኢኮኖሚ ችግር ምልክት መሆኑን ለማወቅ፣ አሲዳማነት የሚጠይቀውን ወጪ፣ እና የአሲድ አፈርን ለመከላከል እና/ወይም ወደ ነበረበት ለመመለስ ወጪዎችን መለየት እና መጠኑን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ከአሲድነት ጋር የተያያዙ ወጪዎች በሁለት ትላልቅ ቡድኖች ሊከፋፈሉ ይችላሉ የሚሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በእርሻ ላይ ወጪዎች እና ከእርሻ ውጭ ያሉ ወጪዎች መሆናቸውን ያብራራሉ።

በእርሻ ላይ የአፈር አሲዳማነት ወጪዎች ዝቅተኛ የሰብል ምርት እና ምርታማ ማስመዝገብ ማለት ነው። በአንዳንድ የአሲዳማነት ሁኔታዎች ይህ ማለት ከአሲዳማነት በፊት በጣም ትርፋማ የሆነው ኢንተርፕራይዝ አነስተኛ ትርፋማ በሆነ የመሬት አጠቃቀም ተተክቷል ማለት ነው።

ምንም እንኳን በአሲድነት ላይ የተደረገው የኢኮኖሚ ጥናት በመጀመሪያ ደረጃ ላይ ብቻ ቢሆንም በግርድፉ ቢሆንም እነዚህ ወጪዎች እንደ ኢኮኖሚ ጉዳትነት ሊቆጠሩ ይችላሉ ብለዋል።

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለፃ የአሲዳማነት ችግርን ለማቃለል በእርሻ ላይ ያሉ አንዳንድ ወጪዎች የበለጠ በእርግጠኝነት እና ትክክለኛነት ሊገለጹ ይገባል። ለምሳሌ፣ በአርሻ መሬት ላይ ያለውን አሲድ ለመቀነስ የኖራ አጠቃቀም ተጨማሪ ወጪ ተሳቢ በማድረግ የኢኮኖሚ ጉዳትን መረዳት ይቻላል ብለዋል።

የአፈር አሲዳማነት የመሬት ሽፋን መቀነስ፤ የውሃ ፍሳሽ እና የአፈር መሸርሸር እድልን ይጨምራል፤ ይህም ደግሞ ግድቦችን ደለልን በመሙላት ጉዳት ሊያደርስ የችላል። ከዚህም በተጨማሪ በመንገዶች ላይ በሚደርስ ጉዳት በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የራሱን ጫና ማሰከተሉ አይቀሬ ነው ይላሉ።

በተጨማሪም ከአሲድነት ጋር የተያያዘውን የናይትሮጅን መለቀቅ የጅረቶች ብክለትን ያስከትላል፤ በዚህም የአካባቢ ወጪዎችን ያስከትላል፤ ከሁሉም በላይ ግን ምርትና ምርታማነት በመቀነሱ ምክኒያት የሚደርሰውነ ያህል ኢኮኖሚያዊ ጫና መለካት ከባድ ነው ይላሉ።

ምሁራኑ ምርታማ መሬትን አክሞ ወደ ምርት በማስገባት ያለውን ኢኮኖሚያዊ ጫና መቀነስ ተገቢ ነው ያሉ ሲሆን በዚሁ ምክንያት ሀገር ከግብርና ማግኘት የሚገባትን ምርት ከማጣቷም ባሻገር በአሲዳማ አፈር ምክንያት የምታወጣውን ያልተገባ ወጪ ለመቀነስ ማህበረሰቡ የአፈር እንክብካቤና ጥበቃ ስራ ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል ብለዋል።

የተሻለ ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ምርት ከለም መሬታችን ይታፈስ ዘንድ የአፈር አስዳማነትን የሚጨምሩ ተግባራትን ከመፈፀም መቆጠብ ይገባል። ከዚህም በላይ ወጪ ቀናሽ የሆኑ የአፈር ማከሚያ ዘዴዎችን በመጠቀመም በአሲዳማ አፈር ምክንያት እየታጣ ያለውን ምርት እንዲጨምር ማድረግ ያስፈልጋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የእንጦጦ ተራራ ጫካና የእንጨት ተሸካሚዋ ምስጢር

**አስመረት ብስራት**



ገና በአፍላ እድሜዋ እንጨት ለቅሞ እና ሸጦ የማደርን ስራ የተለማመደችው ልጅ እንጨት ለቀማ የእድሜ ልክ ስራዋ ሊሆን እንደሚችል አላሰበችም ነበር። አንድ ቀን የተሻለ ነገር ይመጣል በሚለል ማልዳ ከቤቷ ወጥታ እንጨት ለቅማ ሸጣ ቤት መግባት የምታውቀው ብቸኛ ስራዋ ነው።

በመዲናችን የወይዘሮዋን ሥራ የሚጋሩ፣ በሚያገኟት አነስተኛ ገቢ ቀሪ ሕይወታቸውን የሚገፉ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሴቶች አሉ። ሴቶቹ ቀን ከሌት ይለፋሉ፣ ይጥራሉ፤ በየቋጥኙ ለእንጨት ለቀማ ጎንበስ ቀና ይላሉ። በአማካይ በአንዴ አርባ ኪሎ ግራም የሚመዝን የማገዶ እንጨት ተሸከመውም አቀበት ይወጣሉ፤ ቁልቁለት ይወርዳሉ።

የእንጨት ተሸካሚ ሴቶች ሕይወት ጣጣው ብዙ ነው። ድካም ልፋቱም እንደዚያው:: ከዚህ ባሻገር ለሰው ሰራሽ ችግሮች ተጋላጭነታቸውም የዚያኑ ያህል የከፋ ነው። ምን ይህ ብቻ የእንጦጦን ጫካ ለሴቶቹ የእለተ ጉርስ ማገኛ ቢሆንም በዛው ለክ ክብራቸወን የሚነካ ማንነታቸውን የሚዳፈረ ድርጊት ይፈጸምባቸዋል::

በሴቶች ላይ የሚደርሰው አካላዊና ሞራላዊ ጉዳቱ የቱን ያህል ዘግናኝ ቢሆንም ጫካው ገብተው እስኪወጡ ድረስ ወይ ገንዘብ ወይም ሴትነታቸው የሚጠይቁ የጫካው ውስጥ ጎሮምሶችና ደን ጠባቂዎች ከስራቸው ክብደት በላይ የየእለት ራስ መታት ሆነውባቸዋል።

የኑሮ ውጣ ውረዱ የዚህን ያህል አስቸጋሪ ነው። ሊቋቋሟቸው የሚከብዱ ችግሮችን መጋፈጡ፤ ለተለያዩ ማህበራዊ ጥቃቶች መጋለጡ ሴቶቹ የሚጠብቋቸው እለታዊ ክስተቶች ናቸው።

በዚህ ዓይነቱ በማያወላዳ የኑሮ ዑደት ውስጥ ሕይወታቸውን እየመሩ ያሉ በርካቶች አሉ። የማገዶ እንጨት ለቅመው፣ ተሸክመውና ሸጠው ቤተሰብ ከማስተዳደር አልፈው ልጆቻቸውን ኮሌጅ ድረስ አስገብተው በማስተማር ለወግ ማዕረግ ያበቁም እንዲሁ። ከዚህ አድካሚ ሥራ ተላቀው በሌላ የተሻለ ሙያ ዘርፍ በመሰማራት በኑሮአቸው ለውጥ ማየትን የጀመሩ ጥቂት የማይባሉም አሉ።

ለዛሬ የሴቶች አምድ ባለታሪክ አድርገን ያቀረብናቸው ሴትን ያገኘናቸው ጉለሌ እንጀራ ማዕከል ውስጥ ነበር። ትናንት የገፉትን የመከራ ዳገት የኋሊት ትተው ነገን ተሰፋ የሚያደረጉት ወይዘሮ ታሪካቸውን አውግተውናል። መልካም ቆይታ።

ወይዘሮ አባይነሽ አበበ ይባላሉ። ከተወለዱባት ጎሃ ፅዮን ወደ አዲስ አበባ የመጡት ገና በህፃንነት እድሜያቸው ነበር። የእናታቸውን እግር ተከትለው አዲስ አበባን የረገጡት እኚህ ሴት እድሜያቸው ወደ ስልሳዎቹ መባቻ ላይ እንደሚገኝ ይገመታል። እኚህ ሴት ሰባት ልጆች ያሏቸው ሲሆን ነፍስ ካወቁ ጊዜ ጀምሮ የሚያውቁትን እንጨት ለቅሞ መሸጥ ስራን የልጆቻቸው ማሳደጊያ ዋና መተዳደሪያቸው አደርገውት ነበር የኖሩት። ኑሮን ለመግፋት ሲሉ ከአውሬ ጋር እየታገሉ እንጨት ለቅመው በመሸጥ ሕይወትን በእንጦጦ ተራራ ላይ እየገፉ የኖሩት እኝህንና ሌሎች እናቶችን ዛሬ በጉለሌ እንጀራ ማዕከል ውስጥ ተደላድለው እየኖሩ ቢሆንም የኋላ ታሪካቸው ግን በእጅጉ አሳዛኝ ነው::

ወደ ጉለሌ እንጀራ ማዕከል ከመምጣታቸው በፊት እኩለ ሌሊት ካለፈ እንቅልፍ ተኝተው እንደማያውቁ ይናገራሉ። ከዘጠኝ ሰአት ጀምረው ተጠራርተው አቀበቱን ወጥተው፤ ቁልቁለቱን ወርደው ቅጠል ጠርገው፤ ጭራሮ ለቅመው ፤ ከእንጨት ቆራጮች የሚተራርፉ የእንጨት ጉራጆችን ለቅመው የገበያው ሰአት ሳያልፍ ተሸክመው ይሮጣሉ። ይህን ተግባር ደግመው ደጋግመው ተመላልሰውበታል። ከልምዳቸው የተነሳ አድካሚው ጋራን በፍጥነት ሲያልፉ ድካም አይታይባቸውም።

ወይዘሮ አባይነሽን የመሰሉ እንስቶች በውድቅት ጨለማ ከጅብና ከወሮበላ ጋር በመተናነቅ ቤተሰባቸው ሰብሳቢ አጥቶ እንዳይበተን ጥረዋል ደክመዋል። የሌላ እጅ ጠባቂ ላለመሆን ላባቸው በጀርባቸው እየተንቆረቆረ ለዚያውም በሸክም ጭምር ክንድ እና እግሮቻቸው እየዛሉ በየጥሻው ባዝነዋል። ያገኟትንም አሳስረው ወጥተው ወርደዋል፤ከመኖሪያ ቀያቸው እንጦጦ፤ ከእንጦጦም ያሰባሰቡትን ይዘው ገዥ አግኝተው እስኪቀናቸው በመሐል ከተማ ሳይቀር ተዛዙረዋል።

ሕይወት ፈተና ብትሆንባቸውም ከእንጦጦ ተሻርከው፤ ብርታትንና ጥንካሬን ተላብሰው በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በየእለቱ እስከ አርባ ኪሎ ሜትር በእግር ጉዞ መመላለሱ የኑሮ እጣ ፋንታ ሆኖባቸዋል። እንጦጦ የየእለት ፈተና ቢሆንባቸውም የእለተ ጉርስ ግን እንካቸሁ ይላቸዋል።

በሸሮ ሜዳ ወፍ ገና አልተንጫጫም፤ ሌሊቱም ቢሆን ለንጋት ሥፍራውን ለመልቀቅ አልተሰናዳም። የቤተሰቡ የእለት ጉርስ የማሰናጃ ወቅት ነውና ወይዘሮ አባይነሽ መኖሪያ ቤታቸው በጢስ ተሟሙቃለች። ከሙቀቱ ውስጥ ወጥቶ መሄድ ባያስመኝም ከእንጦጦ ጋር የያዙት ቀጠሮ እንዳይረፍድ መሮጥ ግድ ሆኖባቸዋል።

የቤት ውስጥ ጣጣውም የወደቀው በወይዘሮዋ ትከሻ ላይ ነው። ቀን ላይ የሚቋደሷትን ስንቅ ቆጣጥረው፣ የሚጠጧትን ውሃ ሸክፈው ፣ የሥራ ትጥቃቸውንም አሰማምረው ሌሊት አሥር ሰዓት ከመሆኑ በፊት ለአድካሚው ስራ መንደራቸውን የኋሊት ትተው ጉዟቸውን ወደ እንጦጦ ጫካ ያደርጋሉ።

ገና በማለዳው የእድሜ መነሻ እናታቸውን ተከትለው ጫካ የወጡት ወይዘሮ እናታቸው እንጨት ለመሰበር ዞር ከማለታቸው ነበር የደፋሪዎች ሰለባ የሆኑት። ገና በአስራ አምስት አመት እድሜያቸው ተደፈሩ:: አባቱን የማያውቁት ህፃን በማህፀናቸው ተሸክመው ለመዝለቅ ተገደዱ::በዚህ ላይ ማህበረሰቡ የሚያደርስባቸው ጫና ቀላል አልነበረም::

ዲቃላ ወለደች ከሚለው ከመንደርተኛው አፍ አንስቶ የጓደኞቻቸው መጠቋቆሚያ እስኪሆኑ ድረስ በሚያሸማቅቅ ሁኔታ ውስጥ ያለፉት ወይዘሮ፤ ልጃቸው ከማንም ልጅ እንዳያንስ ቀድመው የጀመሩትን ስራ እየሰሩ ለብቻቸው ልጃቸውን በቆራጥነት ማሳደግ ጀመሩ።

ማልደው ከአውሬ ጋር እየተጋፉ ተራራውን መወጣቱ፤ በየመንገዱ ቆመው የሚጠብቋቸው የጫካውን ካቦዎች በገንዘብ ማለፉ፤ ሰው ተተናኮለኝ አልተተናኮለኝ የሚለውን ሰቆቃን መሻገሩ እንዳለ ሆኖ እንጨት የሚሸጡበት አራት ኪሎ ቤተመንግስት አካባቢ ፊት በር እየተባለ የሚጠራው ሰፈር አራት ሰአት ሳይሞላ ለመድረስ የነበረውን ሩጫ ያስታውሳሉ።

"አራት ሰአት ከሞላ ቦታው ላይ የጉሊት ንግድ ይሰራ ስለነበር እነሱ መጥተው ሳያባረሩን መቅደም ነበረብን፤ ካልቀደምን ግን እንጨቱ ሳይሸጥ እንዳይመለስ በጀርባችን ተሸክመን መንደሩን በሙሉ ስናካልል ነበር የምንውለው" ይላሉ።

መንደርተኛው እንጨት ካልፈለገ ከእንጨት ለቃሚዎቹ ሴቶች ተረክበው ለሚቸረችሩ ሰዎች ከዋጋ በታች በመሸጥ፤ ለልጆች የሚሆን ነገር ቋጥረው በአስራ አምስት ሳንቲም አቶቢስ ተሳፍረው ወደ መንደራቸው እንደሚመለሱ ያስታውሳሉ።

የመጀመሪያውን ልጅ ለብቻቸው በጥንካሬ ሲያሳድጉ የተመለከቷቸው ጥበበኛው ባለቤታቸው የትዳር ጥያቄ ያቀርቡላቸዋል። ቀድሞ የደረሰባቸው ቁስል ያልደረቀላቸው እኚህ ሴት በእንቢታ ቢፀኑም፤ ወዳጅ ጎረቤቶቻቸው ከአንድ ሁለት ይሻላል ትዳር መተጋገዣ ነው እያሉ በመምከር ወደ ትዳር ህይወት እንዲገቡ ያደርጓቸዋል።

በወቅቱ ለብቻቸው ታግለው ልጃቸውን ሲያሳድጉ የሞላላቸው ባይሆኑም ምንም አልጎደለባቸውም ነበርና ትዳር ቢያስፈራቸውም ተጨማሪ ልጆች ለመውለድ፤ ብሎም አጋር ለማግኘት በማለት አገቡ።

ባለቤታቸው በሽመና ስራ እሳቸው እንጨት ለቅሞ በመሸጥ ኑራቸውን ለማቅናት ደፋ ቀና ሲሉ የኖሩ ሲሆን በትዳራቸውም ስድስት ልጆችን ለማፍራት በቅተዋል። እርጉዝ ሆነው እንኳን ጓዳቸው እንዳትጎድል ሲሉ የእንጦጦን ተራራ ሳይረግጡ እንደማይወሉ የሚናገሩት ወይዘሮዋ፤ የዛሬ አስር አመት አካባቢ አደጋ እስኪደርስባቸው ድረስ ለአመታት እንጨት ለቅመው ሸጠዋል።

አንድ ቀን እንደልማዳቸው ለቤተሰቦቻቸው አስፈላጊውን ነገር አሰናድተው በጠዋት ከቤታቸው ይወጣሉ። በእለቱ በለስ ቀንቷቸው እንጨት ቆራጮች ሲቆረጡ መሬት የወዳደቀ ጉቶ በብዛት አግኝተው በመዳበሪያ ሞልተው ለገበያ ለመድረስ ጣደፍ ጣደፍ ሲሉ ነበር ወድቀው ክፉኛ የተጎዱት፤ የአጥንት መሰበር የገጠማቸው እኚህ ሴት አጥንቱ እስኪገጥም ድረስ ቤት ዋሉ።

በወቅቱ ልጆቻቸውም ደርሰው ስለነበር ባገኙት ገንዘብ ለአጥንት መጠገኛ እያሉ ሲመግቧቸው፤ ከስራ ተነጥሎ የማያውቀው ገላቸው ሲያርፍና ሌሎች ምክንያቶች ተጨማምረው የስኳር ታማሚ ሆኑ። በዚህ ምክንያት ከልጅነት እስከ እውቀት ከሚሰሩት ስራ ተለያይተው ቤት ቀሩ።

በዚህ መካከል ጤናቸው እየተመለሰ ሲሄድ አንድ የአካባቢው ልጅ ቀበሌ ውስጥ ለሳቸው የሚሆን ስራ መኖሯን ነግሮ ወደ ወረዳ ፅህፈት ቤት እንደወሳደቻውና እዛም የማስተባበር ስራን ሲሰሩ መቆየታቸውን ያብራራሉ።

በሽመና የሚተዳደሩት ባላቸው አቅም እየደከመ ሲሄድ ለመኖሪያ የሚከፈል ሲጠፋ ወደ ባላቸው ዘመዶች ተጠግተው መኖር እንደጀመሩ የሚናገሩት ወይዘሮዋ ልጆቻቸው እድገው ራሳቸውን ቢችሉም ለእርጅና ዘመን መጦሪያ ያለማፍራታቸው ሁልጊዜ ሆዳቸውን እንደሚበላቸው ይናገራሉ።

ልጆቻቸው ገሚሶቹ አረብ ሀገር ደርሰው የመጡ ያሰቡትን ያህል ኑሮ ያልሞላላቸው መሆኑን ይናገራሉ። ገሚሶቹ ደግሞ በአነስተኛ ስራዎች ላይ ተሰማርተው የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ደፋ ቀና የሚሉ ናቸው። የመጨረሻው ልጃቸው አሁን አስራ ዘጠኝ አመቱ ሲሆን በስተመጨረሻ ያገኙት ልጅ ጥሩ ውጤት አምጥቶ አሁን የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ መሆኑን ያስረዳሉ።

የአራት ወንዶችና የሶሰት ሴቶች እናት የሆኑት እኚህ ሴት ዳግም ሌሎች ሴቶች ወደዚህ ህይወት እንዳይገቡ መንግሥት ኃላፊነትን መወጣት አለበት ይላሉ። እኚህ እናት አሁን የተጀመረው በጎ ጅማሬ መቀጠል እንዳለበት ይናገራሉ።

አሁን ላይ በአዲስ አበባ በሁለት ቦታ የተከፈቱት እንጀራ መጋገሪያ ማእከላት በውስጣቸው በርካታ ስራ እየፈለጉ ያጡ፤ ብሎም በጥረታቸው ልጆች ለመሳደግ የሚታገሉ፤ እንጨት ከመሸከም አንስቶ ልብስ እስከ ማጠብ በየሰው ቤት እየዞር ከባባድ ስራዎችን በመስራት ኃላፊነታቸውን የሚወጡ ሴቶችን ይደግፋል ብለው እንደሚያምኑ ይናገራሉ።

እነዚህ ሴቶች በድካምና በጉስቁልና ያለ እድሜያቸው እንዳይሞቱ፤ በህመም ቤት ውለው ለቤተሰብም ሆነ ለሀገር ሸክም እንዳይሆኑ እንደ እንጀራ መጋገሪያ ማእከሉ አይነት የተለያዩ በአቅማቸው ሰርተው ጥሪት የሚያፈሩባቸውን ተቋማት ማዘጋጀት ተገቢ መሆኑን ይናገራሉ።

ከጉለሌ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ድረ ገፅ ባገኘነው መረጃ መሰረት ከንቲባ አዳነች አቤቤ በጉለሌ ክፍለ ከተማ እንጦጦ አካባቢ የተገነባውን የጉለሌ የተቀናጀ የልማት ስራዎችን በማስመረቅ ለአገልግሎት ክፍት አድርገዋል። ከእነዚህ ማእከላትም መካከል ጉለሌ እንጀራ ማዕከል አንዱ ነው።

ፕሮጀክቶቹ በዋነኛነት በአካባቢው እንጨት ከጫካ በመልቀም ለሚተዳደሩ የአካባቢው ነዋሪዎች የስራ እድል የሚፈጥሩ ሲሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጀምረው የተጠናቀቁ የልማት ስራዎች ናቸው::

ጉለሌ እንጀራ ማዕከል ለመዲናዋ ከለሚ ኩራ የእንጀራ ማዕከል በመቀጠል ሁለተኛው የእንጀራ ፋብሪካ ሲሆን በዋነኛነት በአካባቢው እንጨት በመልቀም ለሚተዳደሩ 551 እናቶች የስራ እድል የፈጠረ ነው።

የእንጀራ ማዕከሉ በውስጡ ሁለት የእንጀራ መጋገሪያ ህንጻዎች ፣ የህጻናት ማቆያ ፣ የእህል ማከማቻ ፣ ወፍጮ እንዲሁም ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን ያካተተ ነው። 450 ዘመናዊ የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ ተገጥሞለታል፤ ዘመናዊ የሊጥ ማቡኪያ ማሽን፤ ዘመናዊ የአብሲት መጣያ ማሽን፤ ሁለት ወፍጮዎች፤ 551 እናቶች በሁለት ፈረቃ ተከፍለው ይሰሩበታል።

በእንጀራ ማዕከሉ ውስጥ የስራ እድል የተፈጠረላቸው እናቶች ከዚህ በፊት በአካባቢው እንጨት በመልቀም ሲተዳደሩ የነበሩ፣ ምንም ገቢ የሌላቸው እና የኑሮ ጫና የበረታባቸው እናቶች ናቸው። ይህ ተስፋ ሰጪ ፕሮጀክት እንደ ወይዘሮ አባይነሽ ያሉትን እናቶች ተስፋ ያለመለመ በመሆኑ ይደግ ይጎልብት ብለናል። ቸር ይግጠመን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

አለባበሳቸውን አሳምረው ባማረና በትልቅ መኪና ከሱቃችሁ ደጅ ላይ ወርደው ‹‹እስቲ ሲጋራውን ስጠን ብለው››፤ ከዚያ ወዲያ ግን የሰጣችኋቸውን የ15 ብር ሲጋራ ቀምተው በመኪናቸው ይሸሻሉ ብላችሁ እንዲያው ለአፍታስ ታስቡ ይሆን? በአዲስ ዘመን ትውስታ ውስጥ ግን ይሄ አለ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ 12 ዓመታትን የሠሩት፤ ኢጣሊያዊ ነጋዴ ሀብት ንብረታቸውን ጥለው ጨርቄን ማቄን ሳይሉ ኮብልለው ሸሽተዋል፤ ባለሀብቱ ነጋዴ የገጠማቸው ምን ኖሯል... ከጳውሎስ ኞኞ አጫጭር ደብዳቤዎች ጋር በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ለትውስታ ቀርበዋል፡፡

### ሲጋራ ከሱቅ ወስደው ሳይከፍሉ በመኪና አመለጡ

አፍንጮ በር ከሚገኘው ሙሐመድ ሼክስሩርና ከድር ኑር ከሚያካሂዱበት የጋራ ሱቅ ውስጥ ስማቸውና መልካቸው ገና ያልታወቀ ሁለት ሰዎች ግምቱ 15 ብር የሆነ 10 ፓኮ ዊንስተን ሲጃራ፤ ባለፈው ሰኞ ምሽት ቀምተው መሄዳቸውን ባለቤቶቹ ገለጡ፡፡ ቅሚያውን የፈጸሙት ሰዎች አንድ ትልቅ ሸንጣም በመኪና ይዘው እንደነበሩ ገልጠዋል፡፡

ቅሚያው በተፈጸመበት ጊዜ፤ በሱቁ ውስጥ ተረኛ ሁኖ ሸቀጥ ይሸጥ የነበረው ከድር ኑር ሲሆን፤ ሁለቱ ሰዎች ከመኪና ውስጥ ሁነው በጣም አንገላተውት እንደነበር አስረድቷል፡፡ በዚህም ወቅት ከድር ከሦስት ቦታ ላይ የመቁሰል አደጋ የደረሰበት መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

ከድር ኑር ከትናንት በስቲያ አደጋው እንዴት እንደደረሰበት እያለቀሰ ሲያስረዳ፤ “ሁለት ሰዓት ላይ አንድ ትልቅ ሰማያዊ መኪና ከሱቅ አጠገብ እየበረረ መጥቶ ቆመና ጥሩንባ ነፋ፡፡ ከሁለቱ ሰዎች አንዱ በሩን እየከፈተና እየዘጋ ያንገራግር ነበር፡፡ እንደገና ጠራኝና አስር ፓኮ ሲጃራ አምጣ ካለኝ በኋላ ወስጄ ሰጠሁት” ሲል አስረድቷል፡፡

ከዚያም “መጀመሪያ ከሾፌሩ አጠገብ የነበረው ሰውዬ ሲጃራውን ተቀበለኝና መኪናውን ለሚነዳው ከሰጠው በኋላ ሾፌሩ ኪሱን መዳበስ ጀመረ፡፡ ትንሽ ቆይቶም፤ ስማ ለሕይወትህ ያሰጋሃል ብሎ ሲናገር ሸሚዙን ስይዘው እየጎተቱ መኪናውን እየነዱ ሔዱ” ብሏል፡፡

በዚህን ወቅት አንገቱ ከመኪናው ውስጥ በመሆኑም ሲጮህ ስላልተሰማ ለጊዜው የጎረቤት እርዳታ በፍጥነት ሊያገኝ አለመቻሉን ከድር ገልጧል፡፡ ከዚህ በኋላ ቅሚያውን የፈጸሙት ሰዎች በግምት አምስት መቶ ሜትር ያህል እየጎተቱ ወስደው የጣሉት መሆኑን፤ ከዚያም ተማሪዎች የመኪናውን የሠሌዳ ቁጥር መያዛቸውን ከድር አስረድቷል፡፡

ወንጀሉ እንደተፈጸመ ከድር ከሥራ ባልደረባው ጋር ሁኖ ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ ሔዶ ያመለከተ መሆኑን ገልጧል፡፡ ወንጀሉ ሲፈጸም ያዩትን ሰዎች በምስክርነት መዝግቦ ለፖሊስ ያቀረበ መሆኑን ጠቅሷል፡ :

**(አዲስ ዘመን ጥቅምት 10 ቀን 1963ዓ.ም)**

### ኢጣሊያዊው ነጋዴ ንብረታቸውን ጥለው ኮበለሉ

በልደታ ወረዳ የአሸዋና የድንጋዮች ኢንዱስትሪ ባለቤት የሆኑት ኢጣሊያዊ ሲኞር ሜሪኒ ቪኒስቶ ንብረታቸውን እንዳለ ጥለው ቤተሰባቸውን ይዘው ግንቦት 22 ቀን የጠፉ መሆናቸውን ከመሥሪያ ቤታቸው የተገኘው ዜና ያስረዳል፡፡

ባለንብረቱ ቤተሰባቸውን ይዘው ግንቦት 22 ቀን እሑድ ጧት በ12 ሰዓት ከቤት የወጡት ላንጋኖ እሔዳለሁ ብለው ለሠራተኞቻቸው ነግረው መሆኑን ታውቋል፡፡

ሠራተኞቹም ሰኞ ዕለት እንደተለመደው የተመደቡበትን ሥራ በማከናወን ላይ እንዳሉ፤ በአምስት ሰዓት ላይ ባለንብረቱ ወደ ኬኒያ የሔዱ መሆናቸውን ሠራተኞቹ ከፀጥታ ተረዱ፡፡

ከዚያም ዕለት ጀምሮ በድርጅቱ ውስጥ የሚሠሩ 29 ሠራተኞች የሚያሠራቸው ከማጣታቸውም በላይ፤ ለማን እንደሚያስረክቡ ግራ ገብቷቸው የግቢውን ንብረት በየተራ በመጠበቅ ላይ መሆናቸውን ገልጠውልናል፡፡

በግቢውም ውስጥ ስድስት ከባድ መኪናዎች፤ የአሸዋ ክምሮችና እንዲሁም በውስጡ ምን እንዳለ ያልታወቁ ዘጠኝ ክፍል ቤቶች ተቆልፈው ይገኛሉ፡፡

በድርጅቱ ውስጥ የሚሠሩትም ሠራተኞች አሠሪው የ2 ወር ደሞዛቸውን ሳይከፍሏቸው የጠፉ መሆኑንና ለንብረቱ ያገባኛል የሚል እንዲቀርብ፤ ባይቀርብ ደግሞ ብዙ ዘመን ያገለገልን መሆናችንን አስመስክረን የአገልግሎት ካሣ እንዲሰጠን ሲሉ ለፍርድ ቤት ያመለከቱ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ እንዲሁም ይህንኑ ለጣሊያን ቆንሲል አመልክተው አያገባንም የሚል መልስ ያገኙ መሆኑም ታውቋል፡፡

ከሠራተኞቹ ለማወቅ እንደተቻለው ሲኞር ቪኒስቶ፤ በዚሁ ሥራቸው ላይ 12 ዓመት እንዳላቸውና ከጀመሩም አንሥቶ አብረዋቸው 12 ዓመት የሠሩ ሠራተኞች ከ20 በላይ እንዳሉ ታውቋል፡፡

...

ባለንብረቱም ከአገር መውጣታቸውን የሰሙት በቤቱ ውስጥ ያለውን ንብረትና የቆሙትን መኪናዎች እንወስዳለን እያሉ 10 የሚሆኑ ሰዎች መምጣታቸውን አስረድተዋል፡፡

**(አዲስ ዘመን ሰኔ 13 ቀን 1963ዓ.ም)**

### አንድ ጥያቄ አለኝ

**-አዘጋጅ ጳውሎስ ኞኞ**

*ከጓደኞቼ ጋር ተቀምጠን ስንጫወት የጂማ ታርጋ ያላቸው 2 መኪናዎች ከፊት ለፊታችን ቆመው አየን። የስሙ አጻጻፍ አንዱ ጂማ ሲል ሌላው ደግሞ ጅማ ይላል። ትክክለኛው የስሙ አጻጻፍ እንዴት ነው?

**ይስሐቅ ቀኖ፤ መልኬ ስማ (ከአጋሮ)**

**(አዲስ ዘመን ነሐሴ 13 ቀን 1963 ዓ.ም)**

-ሁለት ዓይነት ስም የሚጽፈው የጅማ ማዘጋጃ ቤት መልሱን ይስጠን እንጂ፤ እኔ ለራሴ የትኛው ትክክል እንደሆነ አላውቅም፡፡

*ዓለም ክብ ናት ይሏታል፡፡ ክብ ባትሆን ኖሮ ግን እንወድቅ ነበር እያሉ ሰዎች ሲናገሩ እሰማለሁ፡፡ ክብ ባትሆን ከምን ላይ እንወድቅ ነበር?

**ዓለም ፀሐይ ገሠሠው(ዓድዋ)**

-ክብ ባትሆን ኖሮ እኛ ብልጦች እንሆንና እንዳንወድቅ ወደ ዳሯ አንሔድም ነበር፡፡ ምናልባትም አንዳንዱ ቀበጥ ቢወድቅ፤ እንደ ቅዱስ ገብርኤል ሰይፍ በአየር ውስጥ ሲንሳፈፍ ይኖር ነበር፡፡

* በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አራት ኪሎ ስድስት ኪሎ እየተባሉ የሚጠሩት ሥፍራዎች በምን ምክንያት በእንዲህ አይነት ስም ሊጠሩ ቻሉ?

**ዘሪሁን ተሰማ**

-አራት ኪሎ አራት ማዕዘን መንገድ ስላለውና፤ ስድስት ኪሎም ስድስት ማዕዘን መንገዶች ስላሉት ይመስለኛል፡፡

**(አዲስ ዘመን ታኅሣሥ 10 ቀን 1963ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ



ደቡብ ኮሪያ እና ጃፓን የሰሜን ኮሪያ ድርጊት የኮሪያ ልሳነ ምድርን ይበልጥ ውጥረት ውስጥ የሚከት ነው በሚል ተቃውመዋል

## ሰሜን ኮሪያ በርካታ ባለስቲክ ሚሳኤሎችን አስወነጨፈች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሰሜን ኮሪያ ዛሬ ጠዋት በርካታ “አጭር ርቀት ተምዘግዛጊ” ሚሳኤሎችን ማስወንጨፏን ደቡብ ኮሪያ ገልጻለች።

ከፒዮንግያንግ አቅራቢያ የተተኮሱት ባለስቲክ ሚሳኤሎች 300 ኪሎ ሜትሮችን ከተጓዙ በኋላ ወደ ምሥራቃዊ የደቡብ ኮሪያ የባሕር ዳርቻ መግባታቸውንም ነው ያስታወቀችው።

ጃፓንም የፒዮንግያንግን የባለስቲክ ሚሳኤል ሙከራ አረጋግጣለች።

የጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ኪሺዳ ጽሕፈት ቤት ባወጣው መግለጫ፥ የአውሮፕላኖች እና መርከቦችን ደኅንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ መረጃዎች በፍጥነት እንዲሰበሰቡ አዟል።

ሰሜን ኮሪያ ባለፉት ወራት እያካሄደችው ያለው የሚሳኤል ሙከራ የኮሪያ ልሳነ ምድር ውጥረትን ይበልጥ ያባብሳል ያሉት ቶኪዮ እና ሴዑል ከአጋራቸው ዋሽንግተን ጋር ትብብራቸውን አጠናክረዋል።

ፒዮንግያንግ በበኩሏ እንደ ሩሲያ እና ቻይና ካሉ ሀገራት ወዳጅነቷን እያጠናከረች ዓለማቀፍ ጫናውን ለመቀነስ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች።

በኅዳር ወር 2023 የመጀመሪያዋን የስለላ ሳተላይት በተሳካ ሁኔታ ያመጠቀችው ሰሜን ኮሪያ፤ በቅርቡ ሁለተኛ ሳተላይት ለማምጠቅ መዘጋጀቷን ደቡብ ኮሪያ አስታውቃለች።

ባለፈው ዓርብ የሞከረችው “ግዙፍ” ክሩዝ ሚሳኤልና አዲስ ፀረ አውሮፕላን ሚሳኤልም ለጎረቤቶቿ ስጋት ፈጥሯል።

ፒዮንግያንግ በሚያዚያ ወር መጀመሪያም “ሃውሶንግ -16ቢ” የተሰኘና ጠጣር ነዳጅ የሚጠቀም አሕጉር አቋራጭ ሃይፐርሶኒክ ሚሳኤል መሞከሯ የሚታወስ ነው።

አረሩን ለማስወንጨፍ ጠጣር ነዳጅ የሚጠቀመው “ሃውሶንግ -16ቢ” አሜሪካን ጨምሮ “በየትኛውም ዓለም የሚገኙ የሰሜን ኮሪያ ጠላቶች”ን በፍጥነትና በኃይል መምታት ይችላል፤ በፀረ ሚሳኤል የመመታት ዕድሉም ዝቅተኛ ነው መባሉ አይዘነጋም።

አሜሪካ፣ ደቡብ ኮሪያ እና ጃፓን የሃይፐርሶኒክ ሚሳኤል ሙከራው የፀጥታው ምክርቤት እገዳን የጣሰ ነው ቢሉም ፒዮንግያንግ ግን እገዳው ሉዓላዊነቴን የሚጥስ እና ራሴን ከአደጋ የመከላከል መብቴን የሚገድብ ነው ትላለች።

የኪም ጆንግ ኡን አስተዳደር ሀገራቱ የሚያደርጉትን ወታደራዊ ልምምድ በሚሳኤል መቃወማቸውንም ቀጥለዋል።

ሩሲያ ባለፈው ወር የመንግሥታቱ ድርጅት በፒዮንግያንግ የኒዩክሌር እና ሚሳኤል ፕሮግራም ላይ የጣላቸው ማዕቀቦች በየዓመቱ እንዲገመገም የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብቷን ተጠቅማ ውድቅ ማድረጓ ይታወሳል።

## ምዕራባውያን መጨረሻው አስከፊ ወደሆነው የኑክሌር ጦርነት እየተንደረደሩ ነው ስትል ሩሲያ አስጠነቀቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር



ምዕራባውያን መጨረሻው አስከፊ ወደሆነው የኑክሌር ጦርነት እየተንደረደሩ ነው ስትል ሩሲያ አስጠነቀቀች።

ሩሲያ፣ አሜሪካ ዩናይትድ ኪንግደም (ዩኬ) እና ፈረንሳይ ለዩክሬን የሚያደርጉት ወታደራዊ ድጋፍ ኑክሌር የታጠቁ የዓለም ኃያላን ወደ ግጭት እንዲገቡ እየገፉ ነው ስትል በዛሬው እለት አስጠንቅቃለች።

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በፈረንጆቹ 2022 በዩክሬን ላይ ያወጁት “ልዩ ወታደራዊ ዘመቻ” ከ1962ቱ የኩባ ኑክሌር ቀውስ ወዲህ በሩሲያ እና ምዕራባውያን መካከል ያለው የዲፕሎማሲ ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀዛቀዝ ማድረጉን የሩሲያ እና የአሜሪካ ዲፕሎማቶች ይናገራሉ።

የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለዩክሬን በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ተጨማሪ ወታደራዊ እርዳታ ካፀደቀ ከሁለት ቀናት በኋላ የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ አሜሪካ እና ኔቶ ሩሲያ ስትራቴጂካዊ ሽንፈት እንዲደርስባት ቋምጠዋል ብለዋል።

ላቭሮብ እንዳሉት ምዕራባውያን ለዩክሬን የሚያደርጉት ድጋፍ አሜሪካ እና አጋሮቿን ከሩሲያ ጋር በቀጥታ እንዲጋጩ ጫፍ ላይ አድርሷቸዋል።

“ምዕራባውያን በአደገኛ ሁኔታ ኑክሌር በታጠቁ የዓለም በኃያላን መካከል ወደሚደረግ እና መጨረሻው አስከፊ ወደሆነ ጦርነት እየተንደረደሩ ነው” ሲሉ ተናግረዋል ላቭሮቭ።

ሩሲያ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ የኑክሌር ጦርነት ሊቀሰቀስ እንደሚችል በተደጋጋሚ ማስጠንቀቋ ይታወሳል።

የአሜሪካ ባለሥልጣናትም ይህን የሩሲያ ማስጠንቀቂያ በትኩረት እንደሚያዩት ሲገልጹ ቆይተዋል።

ዩክሬን እና ምዕራባውያን አምባገነኗ ሩሲያ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚመሳሰል መሬት የመቀማት ጦርነት እያካሄደች ነው፤ በዩክሬን ያለው ኃይሏም ሽንፈት መከናነብ አለበት ይላሉ።

ሩሲያ ይህን ጦርነት የጀመረችው የምዕራባውያን ወታደራዊ ጥምረት የሆነው ኔቶ ወደ ቀድሞ የሶቭየት ሀገራት እየተስፋፋ መሆኑን እና ይህም ለደኅንነቷ እንደሚያሰጋት ከገለጸች በኋላ ነበር።

ሩሲያ በምሥራቅ ዩክሬን የሚገኙ አራት ግዛቶችን በከፊል ወደ ግዛቷ የጠቀለለች ሲሆን ግዛቶቹን ሙሉ ለሙሉ ለመጠቅለል አሁንም እየተዋጋች ትገኛለች።

# ስፖርት




## ‹‹በአፍሪካ ጠንካራ የባሕል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ለመፍጠር ይሠራል››

-አምባሳደር መስፍን ቸርነት

ዓስማየሁ ግዛው



የባሕል ስፖርት ዓለም አሁን ለደረሰችበት የስፖርት እድገት መሠረት በመሆን ጉልህ ሚናን ተጫውቷል። ይህም የሆነው በጠንካራ ብሔራዊ ፌዴሬሽንና የሕዝብ ጠንካራ ተሳትፎ ውጤት እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ኢትዮጵያ በባሕል ስፖርቶች የታደለች ብትሆንም በጥናት ተለይተው እና ሕግ ወጥቶላቸው እየተዘወተሩ የሚገኙት በጣት የሚቆጠሩት ብቻ ናቸው። ለዚህም የተደራጀና ጠንካራ ብሔራዊ ፌዴሬሽን አለመኖሩ ስፖርቶቹ በብዛት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይገቡና የሚፈለገውን እድገት እንዳያሳዩ አድርጎ ቆይቷል።

ለስፖርቱ እድገት የተቋሙ ማደግ አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያ ባሕል ስፖርቶች ፌዴሬሽንና የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር በጋራ ለመሥራት ወጥነዋል።

የኢትዮጵያ ባሕል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ አልፎ በምሥራቅ አፍሪካ ብሎም በአፍሪካ ትልቅ እና ጠንካራ ለማድረግ በፌዴሬሽኑና በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩል እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። የባሕል ስፖርት የተቋቋመበት ራዕዩ ሕዝባዊ መሠረት ለማስያዝ፣ ስፖርቱን ማሳደግና ማጎልበት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ አድጎ ማየት ቢሆንም ያለ ጠንካራ ተቋም ሊታሰብ አይችልም።

የኢትዮጵያ ባሕል ስፖርቶች ፌዴሬሽን በባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ተመዝግበው ከሚንቀሳቀሱ ፌዴሬሽኖች አንዱ ሲሆን ስፖርቶቹን በጥናትና ምርምር በማሳደግና አልምቶ ወደ ዘመናዊ ደረጃ ለማሸጋገር ታስቧል።

የስፖርት ዘርፍ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ ኢትዮጵያን በምሥራቅ አፍሪካና በአፍሪካ የባሕል ስፖርት መነሻና ትልቅ ፌዴሬሽን ፈጥራ እንድትወጣ የመንግሥት ጽኑ ፍላጎት እንዳለው ተናግረዋል። በመሆኑም የሀገሪቱን የባሕል ስፖርት ፌዴሬሽን የማጠናከርና በምሥራቅ አፍሪካና በአፍሪካ ጠንካራ የባሕል ስፖርት ፌዴሬሽን ለማድረግ ጥረት ይደረጋል ብለዋል። ለዚህም ከሚመለከታቸው አጋሮች ጋር በጥናትና በተለያዩ እውቀቶች በማስደገፍ ኢትዮጵያ የባሕል ስፖርት ማዕከል እንድትሆን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ የስፖርት ፖሊሲ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ መሠረት ስፖርቱ ጠንካራ ሆኖ በአሕጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲወጣ የሚቻለውን ድጋፍ እንደሚያደርግም አምባሳደሩ ገልጸዋል። ኢትዮጵያ በባሕል ስፖርት የአፍሪካ ጽሕፈት ቤት ብትመሠርትና ውድድሮችን ብታዘጋጅ ለስፖርቱ እድገት እገዛ ይኖረዋል የሚል እምነት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዘንድ እንዳለ በመጠቆምም ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ እንደተያዘ አስረድተዋል።

እንደ አምባሳደር መስፍን ገለፃ፣ ለስፖርቱ ዕድገት የሚያግዙትን ሰነዶች በማዘጋጀት እና ከአጋር አካላት ጋር በምሥራቅ አፍሪካ እና በአፍሪካ በባሕል ስፖርት ዕድገት ላይ ለመሥራት መንግሥት ጠንካራ አቋም አለው። የመጀመሪያው ሥራ የሚሆነውም በኢትዮጵያ ያለውን እምቅ የባሕል ስፖርት አጥንቶ መለየት ይሆናል። ይህም ስፖርቱ በሌላው ዓለም ለሀገራዊ ጥቅል ምርቱ የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ ለማሳደግ ይረዳል።

የኢትዮጵያ ባሕል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ሕይወት መሐመድ በበኩላቸው፣ ስፖርቱን ለማሳደግና ወጣቶችን በቴክኖሎጂ ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በትብብር በማቀድ የተለያዩ ጥረቶች እንዳሉ ተናግረዋል። በትምህርት ቤቶች የታዳጊ ፕሮጀክቶች ጅምር ሥራዎችን በሁሉም ክልልና ከተማ አስተዳደር ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አስረድተዋል። በተለያዩ ሀገራት የሚገኙትን ትውልደ ኢትዮጵያውያንን የሀገራቸውን የባሕል ስፖርት እንዲያውቁ የሚደረግበት ሁኔታም ይፈጠራል ብለዋል።

ስፖርቱ አድጎ እና ኢትዮጵያ የባሕል ስፖርቶች ማዕከል እንድትሆን የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት የጠቆሙት ፕሬዚዳንት፣ ፌዴሬሽኑ አሁን ያለበትን የበጀት ውስንነት ለመቅረፍ ስፖርቱን ሕዝባዊ መሠረት ለማስያዝ የሚሠራ ቢሆንም በገንዘብ ሊደገፍ እንደሚገባው አብራርተዋል። ውድድር የሚደረግባቸው አስራ አንዱን የባሕል ስፖርት ዓይነቶችን ለማሳደግና በአፍሪካ ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲኖራቸውና ተዘውታሪ እንዲሆኑ በጋራ መሥራት ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል። በዚህም መሠረት በቀጣይ የአፍሪካ ሆኪይ ፌዴሬሽን አባል ለመሆን እንደሚሠራ ጠቁመዋል። ከአፍሪካ አንዱና ጠንካራ ፌዴሬሽን ለማድረግ አባል ለመሆንም የገና ጨዋታን የማዘመን ሥራም በትኩረት ይሠራል። የኦሊምፒክ ስፖርቶች የሆኑትን ከኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ጋር በመተባበር ለማሳደግ ጥረት እንደሚደረግም ገልፀዋል።

### ኦሮሚያ ክልል

ከሳሽ፡- ወ/ሮ ቅድስት ይሳቅ እና ተከሳሽ አቶ ቴዲ ገብረሥላሴ መካከል ያለውን የውል ክርክር አስመልክቶ ተከሳሽ መከሰሳችሁን አውቃችሁ መልሳችሁን አዘጋጅታችሁ በቀነ ቀጠሮ 18-08-2016ዓ.ም ከረፋዱ 4:30 ሰዓት ላይ እንድታቀርቡ የማታቀርቡ ከሆነ መልሳችሁን የመስጠት መብት ታልፎ በሌላችሁበት የሚወሰን መሆኑን የአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል።

**በአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤተሰብ እና የሕፃናት ጉዳይ ችሎት**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም አቶ ተሰማ ዶባሞ አቢዩ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-A00857 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNB2HD249150 ሞዴል ZZ3257N3447A የሞተር ቁጥር WD615.69*170717018267* የሊብሬ ቁጥር 0251034 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 14/8/2016 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገፄዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማላገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፡ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

### ሪቨርስ ቫሊ ኤድብል ኦይል ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ማፍረስ ማስታወቂያ

የሪቨርስ ቫሊ ኤድብል አይል ማኑፋክቸሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አባላት ታህሳስ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ባደረጉት ስብሰባ ማህበሩ እንዲፈርስ ወስነዋል ፡፡ በውሳኔውም መሠረት የማህበሩን ሂሳብና ንብረት እንዲያጣራ ጌታቸው ዱንፊታ የተፈቀደለት ኦዲተር ተሹሟል፡፡ ለዚህም ከዚህ ማህበር ሊከፈለኝ የሚገባ ገንዘብ አለ የሚል ወይም የዚህ ማህበር መፍረስ የሚመለከተውና ባለመብት የሆነ ወገን ሁሉ የእዳ ጥያቄውን በበቂ ማስረጃ በማስደገፍ ይህ ማስታወቂያ በወጣ በ15 ቀን ውስጥ ሂሳቡን ወዳጣራው አካል አድራሻ በስልክ ቁጥር 0940-27-27-35/0911-92-79-97 በመደወል አልያም ቦሌ መድኃኒዓለም አቢሲኒያ ሕንፃ 1ኛ ፎቅ በአካል በመገኘት እንዲያቀርቡ እናሳስባለን፡፡

**ጌታቸው ዱንፊታ የተፈቀደለት ኦዲተር**

### የጨረታ ማስታወቂያ

የመህል ድሬዳዋ መሰረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ንብረት የሆነች ባለ ድርብ ተግባር ሚትሱቡሺ የተሰራበት ሀገር ጃፓን የተሰራበት ዘመን እ/ኤ/አ/1990 ፒክአፕ ደብል ጋቢና መኪና አወዳድሮ ለመሸጥ ቤተክርስቲያን ትፈልጋለች፡፡

መኪናዋን ከሚያዝያ 16/2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 30/2016 ዓ.ም ድረስ መመልከት ይቻላል፡፡ የጨረታ ማስከበሪያ በመህል ድሬዳዋ መሰረተ ክርስቶስ ቤ/ክ ስም በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ በማስያዝ መጫረት ይችላሉ፡፡ የማስያዣ ዋጋው የጨረታው መነሻ 20 በመቶ ሲሆን ዝቅተኛው የመኪናው የማስያዣ ዋጋ 20,000.00 ነው፡፡

ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ሚያዝያ 30/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት በመሐል ድሬዳዋ መሰረተ ክርስቶስ ቤ/ክ ግቢ ለዚሁ በተዘጋጀ ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

ጨረታው ግንቦት 1/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመህል ድ/ዳ መሰረተ ክርስቶስ ቤ/ክ ግቢ ውስጥ ይከፈታል፡፡

በጨረታው ተሸናፊ ለሚሆኑት ተወዳዳሪዎች የጨረታው ማስከበሪያ ጨረታው ከተከፈተበት ከአንድ ቀን በኋላ ተመላሽ የሚደረግ ሲሆን አሸናፊው ግን ሂሳቡን በገዛው ንብረት ላይ የሚታሰብ ይሆናል፡፡

ጨረታውን ያሸነፈው መኪናውን ባለበት ሁኔታ ተረክቦ በአንድ ቀን ውስጥ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ቤተክርስቲያኗ የተሻለ መንገድ ካገኘች ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የተመሰረዝ መብቷ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 251-11-16-13 መጠየቅ ይቻላል፡፡

**መሐል ድሬዳዋ መሰረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን**